# መጽሐፍ ቅዱሳዊ አምልኮና ዝማሬ

## I. መጽሐፍ ቅዱሳዊ/ ክርስቲያናዊ አምልኮ ምንድነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በቀለም ትምህርት እንደምናገኘው ዐይነት የአምልኮን መደበኛ ብያኔ (definition) ባይሰጠንም ከዘፍጥረት እስከ ራእይ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ስለ አምልኮ ያስተምራል። እንዴት? አምልኮ በዋናነት በግንኙነት ይገለጣል፦ ሰው ከእግዚአብሔር ጋርና ሰው ከባልንጀራው ጋር በሚያደርገው ግንኙነት። ከአቤልና ከቃየን ጀምሮ መላው መጽሐፍ ቅዱስ የሚተርከው ይህንኑ ሁለት አቅጣጫ ያለው ግንኙነት ነው። ዐሥርቱ ትእዛዛትም ከዚሁ ዐቅጣጫ ለሁለት የተከፈሉ ናቸው፦ ከትእዛዝ 1-4 ያሉት ሰው ከአምላኩ ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት ይናገራሉ፤ ከትእዛዝ 5-10 የሚገኙት ደግሞ ሰው ከሰው ጋር ሊኖረው ስለሚገባ ግንኙነት ይናገራሉ። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ የአምልኮ መጽሐፍ ነው ማለት ይቻላል የምንለው። አምልኮ፣ ሰው ከአንዴም ሁለቴ (በመጀመሪያው አዳም በሥጋና በሁለተኛው አዳም በክርስቶስ በመንፈስ) የተፈጠረለት፣ የሚኖርለትና ለዘላለም የሚቀጥለው አገልግሎት ነው።

### 1.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብያኔዎች

ሀ. አምልኮ የመጀመሪያው ትእዛዝ ነው። ከዐሥርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያውና ሁለተኛው አምልኮን የተመለከተ ነው። ‹‹ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ… ለራስህ ጣዖታትን አታብጅ፣ አትስገድላቸውም፤ እኔ ቀናተኛ አምላክ ነኝ›› (ዘፀ 20፡ 3-5፤ እንዲሁም ማርቆስ 4፡10)።

ለ. አምልኮ ታላቁ ትእዛዝ ነው፦ ‹‹እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው። አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ኀይልህ ውደድ›› (ዘዳ. 6፡4፣እንዲሁም ማር 12፡28)። በዚህ ቦታ ውደድ የሚለ ውን ቃል አምልክ በሚል ቃል ያለምንም ችግር መቀየር እንችላለን። እግዚአብሔርን እንድንወድበት በተጠየቅነው መሠረት ከእግዚብሔር ውጭ ማንኛውንም ነገር ብንወድ ጣዖት እያመለክን ነው::

መውደድ ጣሪያውን ሲያልፍ አምልኮ ነውና።

ሐ. አምልኮ ራስን ቅዱስና ሕያው መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር መስጠት ነው (ሮሜ 12፡1)። ሐዋርያው ጳውሎስ አምልኮ ማለት ሰውነትን እንደ ቅዱስና ሕያው መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር መስጠት ነው ይላል። ሌሎች ስጦታዎችና አገልግሎቶች ሁሉ የሚጀምሩት ራስን በመስጠት ነው። ራስን ሳይሰጡ በፊት የትኛውንም ስጦታም ሆነ አገልግሎት ለእግዚአብሔር መስጠት አይቻልም። ቢሰጥም ተቀባይነት የለውም።

#### 1.1.1 ተግባራዊ አምልኮ

ንጹሕና ነውር የሌለበት አምልኮ = ተግባራዊ/ በሥራ የሚገለጥ አምልኮ
አምልኮን አስመልክቶ ለድርድር የማይገባ፣ በብሉይም በአዲስም አጽንዖት የተሰጠው እውነት አምልኮ በተግባር፣ በሥራ፣ በኑሮ፣ በሕይወት ዘዬ የሚገለጽ መሆን እንዳለበት ነው። ይህ ሳይሆን ሲቀር እግዚአብሔር የብሉይ ኪዳኑን መሥዋዕት ‹‹የመሥዋዕታች ሁን ፋንድያ በፊታችሁ ላይ እበትናለሁ›› (ሚልክያስ 2፡3)። እንዲሁም በዚሁ መጽሓፍ ‹‹በመሠዊያዬ ላይ እሳትን በከንቱ እንዳታቃጥሉ፣ ከእናንተ ዘንድ ደጅ የሚዘጋ ሰው ምነው በተገኘ! በእናንተ ደስ አይለኝም፤ ቁርባንንም ከእጃችሁ አልቀበልም›› (ሚልክያስ 1፡10)። ጌታም በአዲስ ኪዳን ከተግባር የተፋታ ሜዳዊ ልማድና ሥርዓት

1 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

ስለሆነ አምልኮ ሲናገር ‹‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው፤ የሰው ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል›› (ማቴ 15፡8) ብሏል።

በአዲስ ኪዳንም ሐዋርያው ያዕቆብ የአዲስ ኪዳን አማኞችን ፦ ‹‹ንጹሕና ነውር የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፣ በዓለም ከሚገኝ እድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው››(ያዕቆብ 1፡27) ይላል። እንዲሁም የዕብራውያን ጸሐፊ ‹‹እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፣ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ ፍሬ በእርሱ እናቅርብለት። ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና›› (ዕብ 13፡ 15፣16)።

ብዙ ጊዜ ወንጌላዊያን አማኞች ‹‹በጸጋ ድነናል›› በሚል ሽፋን በጎ ሥራ ለመሥራት፣ ለድኾች ለመቁረስና ለመቆረስ ብዙ ተነሣሽነት እንደሌለን እንታማለን። ብዙ ዋጋ ከፍለው ከጥልቅ ድኅነታቸው እንኳን የሚያካፍሉ ወንጌላዊያን አማኞች ስላሉ ሁሉን በጅምላ የሚኮንን ግርድፍ ማጠቃለያ ምን ጊዜም ትክክል ሊሆን አይችልም። ያም ሆኖ አባባሉ ብዙዎችን በሚመለከት እውነትነት አለው።

የአዲስ ኪዳኑ መሥራችና ሊቀ ካህኑ ጌታ ግን በጸጋ ድናችኋልና ምንም በጎ ነገር አትሥሩ አላለም። በማቴዎስ ወንጌል 25፡ 31-46 ሕዝቦች ሁሉ በፊቱ ለፍርድ እንደሚሰበሰቡ ይናገራል። ለሁለት ይከፈላሉ። በጎችና ፍየሎች ተብለው። በስተቀኙ የሚገኙትን በጎቹን ‹‹እናንተ የአባቴ ቡሩካን ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።›› ይላቸዋል። ምክንያቱን ሲገልጽ ‹‹ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፣ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፣ ታስሬ ወደ እኔ መጥታችኋልና›› ይላቸዋል። በስተግራው የሚገኙትን ፍየሎች የዚህን ግልባጭ ይበይንባቸዋል፦ ‹‹እናንተ ርጉማን፣ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።›› ለምን? በጎቹ ያደረጉትን ሳላላደረጋችሁ ነው መልሱ። ‹‹ኩቶ አላወቅኋችሁም እናንተ ዐመጸኞች ከእኔ ራቁ›› (ማቴ 7፡23) መባልም አለ። ‹‹የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ. kj እንደ ሥራው ያስረክበዋል›› (ማቴ 16፡27)። ለዚህ ነው ስለ አምልኮ ስናስብ በሳምንቱ አንድ ጊዜ በአንድነት ሆነን በጉባኤ ስለምናደርገው ነገር ብቻ ማሰብ የሌለብን። መላ ሕይወታችን፣ መላ ኑሯችን፣ መላ ሥራችን አምልኮ እንደሆነ፣ ለእግዚአብሔር እንደ መሥዋዕት የሚቀርብ እንደሆነ በማሰብ ልንመላለስ ይገባል።

### 1.1.2 ሰው ለምን ያመልካል?

መልሱ ባጭሩ አለማምለክ ስለማይችል ነው። ወደደም ጠላም፣ ፈለገም አልፈለገም ሰው ያመልካል። በመሆኑም እከሌ ያመልካል ወይስ አያመልክም? አይባልም። እከሌም እከሊትም የግድ ያመልካሉ። ጥያቄው መሆን ያለበት እከሌ ወይም እከሊት ማንን ወይም ምንን ያመልካሉ? ነው። ሰው አምላኩን ይመርጣል እንጂ አላመልክም ማለት አይችልም። አምላክ የለም፤ አምልኮም የለም፤ የሚሉ ኮሚኒስቶችና ‹‹ኤቲይስቶች›› የተሰጡ አምላኪዎች ናቸው። ምክንያቱም ብዙ ክርስቲያኖች ለጌታቸው ካላቸው መሠጠት በሚበልጥ መሰጠት ለሚያመልኩት ፍልስፍና ራሳቸውን ያለ መሰሰት ሲሠጡ በእኛም ሐገር ታይቷል።

በምድር ላይ ካሉ ፍጥረቶች ሁሉ መካከል የአምልኮ ዐቅምና ዝንባሌ ያለው ሰው ብቻ ነው። ከየት መጣሁ? ለምን እኖራለሁ? መጨረሻዬስ ምንድነው? ብሎ የሚጠይቅ ፍጡር ሰው ብቻ ነው። የስነ ምግባር ጥያቄ፣ የሚወቅስ ኅሊና ያለው ሰው ብቻ ነው። ሌሎች እንስሳት በደመ ነፍስ ይመላለሳሉ። እንስሳዊ ፍላጎታቸው ከተሟላ ሌላ አስፈልጎት የላቸውም። ስለ ዘላለም አያስቡም፣ ከየት መጣሁ? ለምን እኖራለሁ? መጨረሻዬ ምንድነው? ስሞት ምን እሆናለሁ? ብሎ የሚጠይቅ የቤትም ሆነ የዱር

እንስሳ የለም። ሰው ግን በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ በመፈጠሩና እግዚአብሔር ለሌሎች ፍጥረታት ያላደረገውን እፍ…ታውን ያካፈለው በመሆኑ በቁሣቁስ ብቻ ጠግቦ ሊኖር አይችልም። በሰው ውስጥ ያለውን ባዶ ነገር የትኛውም ዐይነት ቁሣቁስ፣ የትኛውም ዐይነት ገንዘብም ሆነ ንብረት፣ የትኛውም ዐይነት ክብር፣ ዝና፣ ጥበብ፣ ዕውቀት ሊሞላው አይችልም። ሰው እግዚአብሔርን ዐውቆ እንደ እንደ እግዚአብሔርነቱ ካለመለከው ይበላል እንጂ አይጠግብም፣ ይጠግል እንጂ አይረካም፣ ይለብሳል እንጂ አይሞቀውም። ስለዚህ ነው ዳዊት ‹‹እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ፤ ስነቃም ክብርህን አይቼ እጠግባለሁ›› (መዝ 17፡15) ያለው። ቅዱስ አውገስጢኖስም ‹‹ጌታ ሆይ አንተ ለራስህ ፈጥረኸናል፣ ነፍሳችን ባንተ እረፍትን እስክታገኝ ድረስ እረፍት አልባ ናት›› ብለዋል።

### 1.1.3 አምልኮ በብሉይና በአዲስ

ሀ. አምልኮ በብሉይ

ከውድቀት በፊት ስለ ነበረው አምልኮ መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ዝርዝር መረጃ ባይሰጠንም፣ የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ህልዎት እንደ ጥሩ ሽማ ተጎናጽፈውት እንደ ነበር መረዳት አያስቸግርም። እግዚአብሔር በገነት ድምፁን በየወቅቱ ያሰማቸው ነበር። ከውድቀት በኋላ ግን ሰው በቀጥታ ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር የማይችል ምውት ሆነ። በእግዚአብሔርና በሰው መሐል የኃጢአት ግድግዳ ቆመ። ስለዚህ ሰው እግዚአብሔርን ለማነጋገር ሲፈልግ ኃጢአተኛና ምውት በመሆኑና ቅዱሱንና ሕያዉን አምላክ በቀጥታ ማነጋገር ስለማይችል የኃጢአት መሥዋዕት ማቅረብ ነበረበት።

የብሉይ ኪዳኑ አምልኮ የአዲስ ኪዳኑ ጥላ ነው። ብዙዎቹ ትረካዎችና ተምሳሌቶች በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሊሆን ስላለው የሚያመለክቱ ናቸው። ይሁን እንጂ በብሉይ ኪዳን የተሰጡ የሞራል ሕጎች በአዲስ ኪዳንም የማይሻሩ አሉ።

ለ. አምልኮ በአዲስ

የአዲስ ኪዳን አምልኮ የብሉይ ኪዳኑ ፍጻሜ ወይም እውነተኛ አካል ነው። የአዲስ ኪዳን አምልኮ መሠረቱ በኢየሱስ ቤዛዊ መሥዋዕትነት ላይ ወይም በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በተሠራው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው። የአዲስ ኪዳኑ አምልኮ በተቀደደው መጋረጃ በክርስቶስ የተቆረሰ አካልና የፈሰሰ ደም አማካይነት በአካል በምድር ሆነን፣ በመንፈስ ገሥግሰን፣ ሰተት ብለን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ገብተን፣ በሰማይ ካሉ መላእክት፣ ቅዱሳት ፍጥረታትና ቅዱሳን ሰዎች ጋር ፊቱን እያየን የምናመልክበትና እርሱን በምምሰል የምንለወጥበት ሂደት ነው (ዕብራውያን 12፡22፤ 2ኛ ቆሮ 3፡18)።

## 1.2 የተለያዩ ሰዎች ለአምልኮ የሰጧቸው ብያኔዎች/ ትርጉሞች

### 1.2.1 የተለያዩ ጸሐፊዎች ስለ አምልኮ

‹‹ማምለክ መላውን ሁለንተናችንን ለእግዚአብሔር ማስገዛት ነው። ኅሊናን በእግዚአብ ሔር ቅድስና ማነቃቃት፣ አእምሮን በእግዚአብሔር እውነት መመገብ፣ ምናብን በእግዚአ ብሔር ውበት ማንፃት፣ ልብን ለእግዚአብሔር ፍቅር መክፈትና ፈቃድን ለእግዚአብሔር ሐሳብ ማስገዛት ነው››

ዊሊያም ቴምፕል

‹‹አምልኮ በግልም በጉባኤም በምንናገረው ነገርና በምንኖረው ኑሮ ለእግዚአብሔር ስለ ማንነቱና ስለ ሠራው ሥራ የምንሰጠው ምላሽ ነው።››

ሉዊ ጊግሊዮ

‹‹አምልኮ ራሴን ሙሉ ለሙሉ ለአንድ ሰው ወይም ለአንድ ነገር በመስጠት በዚያ ነገር ቁጥጥር ሥር ለመሆን ያለኝ ፍላጎት ምልክት ነው።››

ሀሮልድ ቤስት

‹‹አምልኮ አማኙ በሁለንተናው ማለትም በአእምሮው፣ በስሜቱ፣ በፈቃዱ፣ በአካሉ፣ ለእግዚአብሔር ማንነትና ስለ ሥራው የሚሰጠው ምላሽ ነው።››

ዋረን ዌርስቢ

‹‹አምልኮ ማለት በሕይወታችን ትልቅ ዋጋ የምንሰጠውንና ከሁሉ በላይ የምንወደውን ነገር ምንነት የሚገልጥ የምናስበው ነገር ሁሉ፣ የምንለው ነገር ሁሉ እና የምናደርገው ነገር ሁሉ ነው።››

ጆሽ ራይሌ

‹‹አምልኮ ማለት ሕይወታችንን እንደማያቋርጥ ሕያው መሥዋዕት አድርገን በግልና በጋራ ለሰው ወይም ለሆነ ነገር መስጠት ማለት ነው።››

ማርክ ድሪስኮል

‹‹አምልኮ ማለት በመረጠኝ አምላክ ፊት አልያም በመረጥኳቸው አማልክት ፊት ያለ ማቋረጥ የማፈስሰው የሆንኩት ሁሉ፣ የማደርገው ሁሉ፣ ልሆን የምችለው ነገር ሁሉ ነው።"

ሀሮልድ ቤስት

‹‹እምነትህ ጠንክሮ፣ ፍቅርህ ጥልቀት ጨምሮ፣ ርኅራኄህ ሰፍቶ፣ ፈቃድህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ይበልጥ ወስኖ ከጉባኤ አምልኮ ከወጣህ በእርግጥ አምልከሃል።››

ፓስተር ኤፍ ዌብ ኬሪ

### 1.2.2 ቀጥሎ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ የብያኔ ሙከራዎች ቀርበዋል፦

በቅድሚያ ዝነኛው እንግሊዛዊው ጸሐፊ ተውኔት ዊሊያም ሼክስፒየር ከተናገራቸውና ብዙዎች ብዙ ጊዜ በሚጠቅሱለት አንድ ዝነኛ ጥቅስ ላይ ተመሥርቶ የተዘጋጀውን ጥቅስ እንመልከት። ጥቅሱ በፈረንጅኛ ‹‹All the world is a stage, and all the men and women merely players/ actors.›› ይላል። ወደ አማርኛ ሲመለስ ‹‹መላው ዓለም የተውኔት መድረክ ነው፤ሰዎች ሁሉ ተዋንያን ብቻ ናቸው›› ማለት ይሆናል። በዚህ ታላቅ የኪነ ጥበብ ሰው ጥቅስ ላይ የተመሠረተ የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ብያኔ ቀጥሎ ያለው ነው፦

‹‹መላው ዓለም የአምልኮ መሠዊያ ነው፤ ሰዎች ሁሉ አምላኪዎች ናቸው››

ቀጥሎ ሌሎች ጥቅሶችን እንመልከት፦

‹‹ዋናው የአምልኮ ቦታ አብዛኛውን ጊዜያችንን የምናጠፋበት ቦታ ነው።››

‹‹እነሆ አምልኮ እዚህ አለ፣ እነሆ አምልኮ እዚያ አለ ቢሏችሁ አትመኑ። አምልኮ በልባችሁ መሠዊያ፣ በውስጣዊው ማንነታችሁ ከሌለ፣ ለእናንተ አምልኮ የትም የለም፣ ምንም ውስጥ የለም።››

‹‹ሰዎች ሊያስዘምሩን፣ ሊያስጨበጭቡን፣ ሊያ ስሸበሽቡን ይችላሉ፣ 'ሊያስመልኩን' ግን አይችሉም። መዘመር፣ ማጨብጨብና ማሸብ ሸብ ብቻቸውን አምልኮን ሊፈጥሩ አይችሉምና። እውነተኛ አምልኮ የብዙ ነገሮች ድምር ውጤት ነው እንጂ በመድረክ ተጀምሮ በመድረክ የሚጨረስ ፐርፎርማንስ አይደለም። ››

‹‹አንዳንድ ሰዎች 'በዚህ ዘመን አምልኮ ሞልቷል፤ ቅድስና ጠፍቷል' ሲሉ ይደመጣል። እርስ በርሱ የሚቃረን አባባል ነው። አምልኮ የመቀደስ መንገድ ነው። ቅዱሱን አምላክ ማምለክም መቀደስ ነው። አምልኳችን ወደ ቅድስና የማያመጣን ከሆነ አምልኮ ብለን ልንጠራው አንችልም።››

## 1.3 መጀመሪያ የመጠቀስ ሕግ ለአምልኮ ብያኔ

የሥነ አፈታት ተማሪዎች፣ አንድ ቃልና ድርጊት መጀመሪያ የተጠቀሰበት ቦታ ያን ቃል ለመተርጎም የሚረዳ ቁልፍ መርሖ ይሰጠናል ይላሉ። በዚህ መሠረት መሥዋዕት የሚለው ቃልና ድርጊት ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው በዘፍጥረት 4 ላይ ነው። በዚህ ቦታ እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ በሁለቱ ወንድማማቾች ስለ ቀረበለት መሥዋዕት አስተያየት ይሰጣል። እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ተቀብሎ የቃየንን መሥዋዕት ያልተቀበለበት ምክንያት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ የምንሰጠው መልስ አምልኮን ለመተርጎም ቁልፍ መርሖ ይሰጠናል። መልሱ እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት የተቀ በለው የአቤልን ሕይወት ስለተቀበለ ነው፤ የቃየንን መሥዋዕት ያልተቀበለው የቃየንን ሕይወት ስላልተቀበለ ነው የሚል ነው። ‹‹እግዚአብሔር ወደ አቤልና ወደ መሥዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መሥዋዕቱ ግን አልተመለከተም›› (ዘፍ 4፡4፣5)። ቁልፉ ቃል ና የሚለው መስተጻምር/ conjunction ነው። በዚህ መሠረት እግዚአብሔር አስቀ ድሞ ያየው የአቤልን ሕይወት ወይም ማንነት ነው። የአቤልን ሕይወትና የሕይወት ዘዬ ባይቀበል ኖሮ የአቤልን መሥዋዕት አይቀበልም ነበር። የቃየንን መሥዋዕት ያልተቀበ ለበትም ምክንያት ሕይወቱ፣ ማንነቱ፣ የኑሮ ዘይቤው ለእግዚ አብሔር መሥዋዕት እንዲያቀርብ የሚያስችለው ስላልነበረ ነው።

### 1.3.1 ከዚህ የምናወጣው መርሖ

‹‹እግዚአብሔር መሥዋዕትን የሚቀበለው መሥዋዕት አቅራቢውን ሲቀበል ነው፤ መሥዋዕት አቅራቢውን ካልተቀበለ እግዚአብሔር መሥዋዕትን አይቀበልም።››

‹‹እግዚአብሔር አገልግሎትን የሚቀበለው አገልጋዩን ሲቀበል ነው፤ አገልጋዩን ካልተቀበለ አገልግሎቱን አይቀበልም።››

‹‹እግዚአብሔር አምልኮን የሚቀበለው አምላኪውን ሲቀበል ነው፤ አምላኪውን ካልተቀበለ አምልኮውን አይቀበልም።››

‹‹እግዚአብሔር ዝማሬን የሚቀበለው ዘማሪውን ሲቀበል ነው፤ ዘማሪውን ካልተቀበለ ዝማሬውን አይቀበልም።››

‹‹እግዚአብሔር ስብከትን የሚቀበለው ሰባኪውን ሲቀበል ነው፤ ሰባኪውን ካልተቀበለ ስብከቱን አይቀበልም።››

 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

አምልኮን ወይም ዝማሬን ከሌሎች ዓለማዊ ሙዚቃዎች ወይም ደግሞ ከዘፈን የሚለየው ዋናው ነገር ይኼ ነው። አንድ ዘፋኝ ወይም ዓለማዊ አርቲስት የሚመዘነው በዘፈኑ ወይም በአርቱ ብቻ ነው። ማንኛውንም ክርስቲያናዊ አገልግሎት እግዚአብሔር እንዲቀበለው ወይም እንደ አምልኮ መሥዋዕት እንዲቆጥረው የሚያደርገው የሚያቀር በው ሰው ማንነት ነው። ዝማሬንም ሆነ ሌላ ማንኛውንም መሥዋዕት ከማቅረብ በፊት በሮሜ 12፡1 መሠረት መላ ሁለንተናን ‹‹ቅዱስ፣ ሕያውና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት›› አድርጎ ማቅረብ ይቀድማል። አለዚያ መሥዋዕቱ ወይም አገልግሎቱ እንደ ቃየል መሥዋዕት ተቀባይነት አይኖረውም ወይም ‹‹ዲስኳሊፋይድ›› ይሆናል።

በኑሯቸውና በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ሳያመልኩት፣ በአምልኮ ቀናት ብቻ ሥርዓቱን በመፈጸም ለማምለክ የሚሞክሩትን ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት የነበሩትን አምላኪዎች ጌታችን ሲወቅስ ‹‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፣ ልቡ ግን ከእኔ እጅግ የራቀ ነው፤ የሰው ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል›› (ማቴ 15፡8) ብሏል። ባጭሩ ከንቱ አምልኮ ማለት ከሕይወትና ከዕለታዊ የኑሮ ዘይቤ የተፋታ ሳምንታዊ ሥርዓት የመፈጸም ወግና ልማድ ነው።

## 1.4 የግልና የጉባኤ አምልኮ

አምልኮን በቅጡ ለመረዳት ቢያንስ ለሁለት ከፍሎ መመልከት ጠቃሚ ነው። አምልኮ በጥቅሉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፦ እነዚህም የግል አምልኮና የጉባኤ አምልኮ በመባል ይታወቃሉ። እስቲ የሁለቱን ትርጉምና ልዩነት እንመልከት፦

### 1.4.1 የግል አምልኮ

የግል አምልኮ በቀን ለ24 ሰዓት፣ በሳምንት ለ7ቀናት በዓመት ለ365/66 ቀናት በሁሉም ስፍራ በእግዚአብሔር ፊት እንደሆንን በማወቅና በመረዳት የምንኖረው ኑሮ ነው። በአጭሩ ሲቀመጥ፦ ***የግል አምልኮ ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ በእግዚአብሔር ፊት እንደሆንን በማወቅና በመረዳት የምንኖረው ኑሮ ነው።*** እንግዲያውስ የግል አምልኮ የተወሰነ ቦታና የተወሰነ ጊዜ የለውም። ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ አምልኮ ላይ መሆናችንን ማወቅ አለብን። ምክንያቱም አምላካችን ሰማይንና ምድርን የሞላ አምላክ ነው፤ እንዲሁም በአዲስ ኪዳናዊ መቅደሱ በእኛ ውስጥ በመንፈሱ አማካይነት አለ። ስለዚህ ከአምልኮ ነጻ (exempted) የምንሆንበት ቦታም ሆነ ጊዜ የለም። እያንዳንዷ እስኩየር ሜትር የአምልኮ ቦታ፣ እያንዳንዷ ማይክሮ ሰከንድ የአምልኮ ጊዜ ነች። የግል አምልኮ በሌላ አገላለጽ የሕይወት ዘዬ አምልኮ (Life style worship) በመባል ይታወቃል።

ለግል አምልኮ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ወጣቱ ዮሴፍ ነው። አንድም ዕብራዊ ባልነበረበት የግብፅ ምድር እንዲሁም ማንም ሰው በሌለበት ቤት ውስጥ ቢሆንም ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እንደሆነ መረዳቱ ነበረው። እናም የጌታው ሚስት ላቀረበችለት የነውር ግብዣ የሰጣት መልስ ‹‹በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአት እሠራለሁ?›› (ዘፍ 39፡9) የሚል ነበር።

### 1.4.2 የጉባኤ አምልኮ

***አማኞች በሳምንት ለተወሰኑ ቀናት፣ ለተወሰኑ ሰዓታት፣ በተወሰኑ ቦታዎች በአንድነት በመሆን እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት፣ እርስ በርሳቸው የሚተናነጹበትና ድነት ላላገኙት ምስክርነታቸውን በስብከተ ቃልና በዝማሬ የሚሰጡበት አገልግሎት ነው።***

ልብ በሉ! የግል አምልኮ የጉባኤ አምልኮ መሠረት ነው። የግል አምልኮ ከሌለ የጉባኤ አምልኮ የለም። ይሁን እንጂ የግል አምልኮ የጉባኤ አምልኮን ሊተካ አይችልም፤ የጉባኤ አምልኮም የግል አምልኮን

ሊተካ አይችልም። ለጤናማ የቤተ ክርስቲያን ሕይወትና አገልግሎት ሁለቱንም በሚዛናዊነት ማስኬድ ያስፈልጋል።

## I.5 ቤተመቅደስ መሥዋዕትና ካህን

### 1.5.1 በብሉይ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን፣ በተለይ እግዚአብሔር ለሙሴ የአምልኮን ሥርዓት ማለትም የቤተ መቅደ ሱን፣የመሥዋዕቱን፣የክህነቱንና መሰል  የአም ልኮ ሕግጋትን ከሰጠው በኋላ እግዚአብሔርን ለማምለክ እነዚህ ሦስቱ ማለትም ቤተ መቅደስ (የመገናኛው ድንኳን)፣ መሥዋዕትና ካህን መኖር ነበረባቸው። ከእነዚህ አንዱ ከተጓደለ አምልኮ አይኖርም ነበር። የሳሙኤ ልን እናት ሐናን ብንወስድ እግዚአብሔርን ለማምለክ፣ ስዕለት ለመሳልና ስዕለቷንም ለመክፈል በየዓመቱ በሴሎ ወደ ነበረው የመገናኛው ድንኳን ወደሚባለው ስፍራ መሄድ ግዴታዋ ነበር። በዓመት ውስጥ ለተወሰኑ ጊዜያት ወደ አምልኮ ስፍራ ሄዶ የበዓሉን ሥርዓት መፈጸም የሁሉም እስራኤላዊ ግዴታ ነበር።

### 1.5.2 በአዲስ ኪዳን

የአዲስ ኪዳን አምልኮ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እግዚአብሔር በሠራው ሥራ ላይ የተመሠረተ ነው። እንደ ብሉይ ኪዳን ጥላና ምሳሌ ሳይሆን እውነተኛ የሆነው አካል የተገለጠበት አምልኮ ነው። የብሉይ ኪዳን ጥላዎች ወይም አምሳያዎች የሚያመለክቱት ወደ ክርስቶስ ነበር። በአዲስ ኪዳን ክርስቶስ ከተገለጠ በኋላ ግን ጥላዎቹ ተሻሩ። የዕብራውያን መጽሐፍ ስለ እነዚህ የተሻሩ ጥላዎች በስፋት ይዘረዝራል። ወደ እነዚያ ሁሉ አሁን ልንገባ አንችልም።

በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እጅግ ትልቅ ለውጥ ከተደረገባቸው የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶች መካከል ዋናው አምልኮ ነው። የአምልኮ ሥርዓቶችና መንገዶች በሞቱና በትንሣኤው በአያሌው ተለውጠዋል። በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ሰው ነው (1ኛ ቆሮ 3፡16)፣ መሥዋዕቱም ሰው ነው (ሮሜ 12፡1)፣ ካህኑም ሰው ነው (1ኛ ጴጥ 2፡9)። ይህም በክርስቶስ ደም የነጻው፣ በመንፈሱ የተቀደሰውና በቃሉ የታጠበው ሰው ነው። የብሉይ ኪዳን አምልኮ ማዕከል ከቁሣቁስ የተሠራ ቤተ መቅደስ ነበር፣ የአዲስ ኪዳን የአምልኮ ማዕከል ግን ሰው ነው።

## I.6 የአምልኮ መልክ እና የጣዖት አምልኮ

እውነተኛ ስለሆነ አምልኮ ካነሣን ዘንዳ፣ እውነተኛ ስላልሆነው አምልኮ በመጠኑ ማንሣት ግድ ነው፣ ምንም እንኳን በቀጥታም በተዘዋዋሪም መንገድ አምልኮ የሚመስሉ ግን ያይደሉ ብዙ ነገሮች እንዳሉ የጠቀስን ቢሆንም ከዚህ በመቀጠል ሁለት ትክክለኛ ያልሆኑ የአምልኮ ዐይነቶችን እንመለከታለን፡- የአምልኮ መልክና የጣዖት አምልኮ ይባላሉ። እነዚህ ሁለቱ እርሰ በርስ የሚወራረሱ እርስ በርስ የሚመጋገቡ፣ ድንበራቸው በውል የማይታወቅ ቢሆንም ቀጥሎ ለየብቻ እንመለከታቸዋለን።

### 1.6.1 የአምልኮ መልክ

1 ከቃየን መሥዋዕት ጀምሮ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር የአምልኮን መልክ ሲቃወም እናገኛለን። የአምልኮ መልክ ማለት መልክ ብቻ፣ ቅርጽ ብቻ፣ ይዘት የሌለው፣ ውስጡ ሲፈተሽ ባዶ የሆነ ማለት ነውalbums. ። በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በቤተ መቅደሱ ወይም በመገናኛው ድንኳን የሚደረገውን አገልግሎትና አገልጋዮች የሚቃወምበትና አምልኮውንም መሥዋዕቱ ንም አልቀበልም የሚልበት ዋና ምክንያት ሜዳዊና ሥርዓቱን ለመፈጸም የሚደረግ እንጂ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበት በመሆኑ ነበር (ይመ 1ኛ ሳሙ 15፡

22-23፣ መዝ 51፡16፣ ምሳ 15፡8 (21፡7)፣ ኢሳ 1፡11-17፣ ኤር 6፡20-21፣ ሆሴዕ 6፡6፣ አሞጽ 4፡4-5፣5፡21-24፣ ሚልክያስ 1፡10፣ 2፡3)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡ 1-6 ላይ የመጨረሻውን ዘመን ምልክቶች ይዘረዝራል።ዘመኑን አስጨናቂ የሚያደርጉትን ወደ 18 ክፉ ባሕርያት ይዘረዝራል። መውደድና አምልኮ በጣም የተቆራኙ ስለሆኑ ከመውደድ ጋር የተገናኙትን ብቻ እንመልከት፡- ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፣ ገንዘብን የሚወዱ…ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤ ይልና በመጨረሻው ***የአምልኮ መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል*** ከእነዚህ ደግሞ ራቅ ብሎ ይደመድማል።

እዚህ ቦታ ላይ ስለ አምልኮ ጥልቅ ምስጢራትን እንማራለን። በመጀመሪያ የምንመለከተው ዐቢይ ሐሳብ አምልኮ ከመውደድ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑን ነው። የመጨረሻው ዘመን ሰዎች ታላቁን ትእዛዝ የመፈጸም ዐቅም ያንሳቸዋል። ምክንያቱም ታላቁ ትእዛዝ ያልተከፋፈለውን፣ የመጨረሻውን ወይም ከሁሉም የላቀውን የመውደድ ዐቅምህን እግዚአብሔርን ለመውደድ አውለው ይላል። የዚህ ዓለም ገዢ የሆነው ዲያብሎስ ደግሞ ረቂቅ በሆነው ተንኮሉ፣ የተለያዩ ዘመናዊ ሚዲያና ማስታወቂያዎችን በመጠቀም ለመጨረሻው ዘመን ሰው ያለማሰለስ የሚሰብከው ስብከት፡- ዓለምን ውደድ፣ በዓለም ያለውን ውደድ፣ ገንዘብን ውደድ፣ ድሎትን ውደድ፣ ከሁሉ በላይ ራስህን ወደድ፣ አልፎ ተርፎም ራስህን አምልክ የሚል ነው።

ይኸ ዐይነቱ መውደድ ደረጃው እጅግ ከፍ ያለ አምልኮ ነው፤ ምክንያቱም ሰው የሚያመልከ ውን ነገር ይወዳልና፤ የሚወደውን ነገርም ያመልካልና ነው። በእርግጥ ሁሉም መውደድ አምልኮ ነው ማለት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ‹‹ውደድ›› ብሎ ያዘናል። ለምሳሌ ባሎች ሚስቶቻችንን፣ ደግሞም አማኞች ሁሉ ባልንጀሮቻችንን እንድንወድ ታዝናል። ይኼ ዐይነቱ መውደድ አምልኮ አይባልም። ነገር ግን መውደድ ደረጃ አለው፣ ጣሪያ አለው። መውደድ ጣሪያውን ሲያልፍ መውደድ መሆኑ ቀርቶ አምልኮ ይሆናል። ይህ ዐይነቱ መውደድ ለእግዚአብሔር የቀረበ ካልሆነ በስተቀር ለሰውም ሆነ ለቁሣቁስ ወይም ለሆነ ነገር ካዋልነው የሚወደደው ነገር ጣዖት ይሆናል፤ ድርጊቱም አምልኮተ ጣዖት ይባላል።

የመጨረሻው ዘመን ሰዎች ባለ በሌለ ኃይላቸው ራሳቸውን ይወዳሉ፣ ገንዘብን ይወዳሉ፣ ተድላን ይወዳሉ። ከዚያ በተረፋቸው የመውደድ ዐቅም እግዚአብሔርን እንወዳለን ወይም እናመልካለን ይላሉ። እግዚአብሔር ደግሞ ይኼ በትርፍራፊ ፍቅር የሚቀርብለትን ሽርፍራፊ ‹‹አምልኮ››፣ አምልኮ ሳይሆን የአምልኮ መልክ ብሎ ሰይሞታል። መልክ ብቻ ነው፤ ኃይል የለውም።

እንግዲያውስ እውነተኛው አምልኮ ኃይል አለው። ከዓለምና ከዓለማዊነት የሚያወጣ፣ የጌታን ምጽአት እየጠበቅን በቅድስናና በጽድቅ፣ ራሳችንን በመግዛት እንድንኖር የሚያስችለን ኃይል አለው። አምልኳችን በሕይወታችን ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ኃይል ከሌለው፣ እውነተኛ አምልኮ እያመለከን አይደለንም። ሜዳዊ ነገሩን ስናይ ለእኛ አምልኮ መሰለን እንጂ አምልኮ አይደለም የአምልኮ መልክ እንጂ ።

### 1.6.2 የጣዖት አምልኮ

በዚህ ዘመን ስለ ጣዖት አምልኮ ሲነሣ ብዙዎቻችን እኛን የማይመለከተን ይመስለ ናል። ምክንያቱም የጣዖት አምልኮ የሚመስ ለን ከድንጋይ፣ ከእንጨት ወይም ከከበሩ ድንጋዮች ለተሠሩ ቅርጻ ቅርጾች ወይም ደግሞ ለተራራ፣ ለወንዝ፣ ለዛፍ፣ ለጨረቃ፣ ለክዋክብት ወዘተ አካላዊ ስግደት ማቅረብ ብቻ ነው። ለእነዚህ መስገድ የጣዖት አምልኮ አይደለም እያልኩ አይደለም፤ ይኼ መደበኛ የአምልኮተ ጣዖት

 

ትርጉም ነው። ነገር ግን ቃሉ ሰው ለተሸነፈበት ለዚያ ተገዝቶ ባሪያ ነው ይላል። በግልባጩ ሰውን ያሸነፈው ያ ነገር፣ ጌታው ወይም አምላኩ ነው ማለት ነው። ኢየሱስ ‹‹ለሁለት ጌታ መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም›› (ማቴ 6፡24) ሲል ባዕድ አምላክን (ጣዖትን) እና እግዚአብሔርን ባንድ ጊዜ ማምለክ አትችሉም ማለቱ ነው።

ማንኛውንም በራሱ ምንም ችግር የሌለበት መልካም ነገር ወደ ጣዖትነት ልንቀየርው እንችላለን። ከእግዚአብሔር ይልቅ የምንወ ደው፣ የምንደገፍበት፣ የምንታመንበት፣ ራሳች ንን የምንጥልበት ማንኛውም ነገር ጣዖት ይሆናል። ገንዘባችን ቢሆን፣ ሆዳችን፣ ቢሆን፣ ክብራችን ቢሆን፣ ዘራችን/ ጎሳችን ቢሆን፣ ዘመዳችን ቢሆን፣ ዕውቀታችን ቢሆን፣ ሥልጣናችን ቢሆን፣ መልካችን ቢሆን ከፋኛ ልንጣበቅበት አይገባም። በእነዚህ ነገሮች ፍቅር ልንነደፍ አይገባም። ሁለንተናዊ ፍቅራችን፣ አቻ የሌለው ፍቅራችን፣ በፍጹም ልብ፣ ነፍስና ኃይል የሆነ ፍቅራችን የሚገባው ነፍሱን እስኪሰጥ ድረስ ለወደደን ለአንዱ ጌታ ብቻ ነው። ይህን ለእርሱ ልንጡብቅለት የሚገባውን ፍቅር ለሌሎች ነገሮች ከሰጠን አመንዝሮች እንሆናለን፤ በሌላ አገላለጽ ጣዖት አምላኪዎች እንሆናለን።

ቀደም ባሉት ዓመታት የሆነ ነገር ላይ ሰዎች ያላግባብ ሲጣበቁ ሲመለከቱ አንዳንድ አማኞች ትልቅ ጥበብ ያለው ምክር ይመክሯቸው ነበር፦

‹ቢዝነስህ ጣዖት እንዳይሆንብህ!››
‹‹ጸጉርሽ ጣዖት እንዳይሆንብሽ!››
‹‹ትምህርትህ ጣዖት እንዳይሆንብህ!
‹‹ልጅሽ ጣዖት እንዳትሆንብሽ!›› ወዘተ ይሉ ነበር።

ምን ማለታቸው ነበር? የእግዚአብሔርን ስጦታ በእግዚአብሔር ፋንታ አታምልከው ወይም ከልክ በላይ አትውደደው ማለት ነው። ለእግዚአብሔር፣ ለፈጣሪ፣ ልትሰጥ የሚገባ ውን ፍቅር ለፍጡር አትስጥ ማለት ነበር። ምናልባት ከሁለት ዐሥርታት ወዲህ ‹‹ይኼና ያኛው ነገር ጣዖት እንዳይሆንብህ! ጣዖት እንዳይሆንብሽ!›› ሲባል ሰምቼ አላውቅም። ሰዎች ጣዖት ማምለካቸውን ስለተዉ ይሆን? ወይስ በድኅረ ዘመናዊው ዘመን የሚኖሩ ሰዎች የፈለጉትን፣ የመረጡትን ማምለክ እንዲችሉ ‹‹ዲሞክራሲያዊ›› መብታቸው ሰለተጠበቀላቸው ይሆን? ወይስ ጣዖታቱ ወደ ሰው ሁለንተና ገብተው የሰውን ሁለንተና ስለ ተቆጣጠሩት የቱ ጣዖት እንደሆነና እንዳልሆነ መለየት ከሚያዳግትበት ጊዜ ላይ በመድረሳ ችን ይሆን? ወይስ ሁሉም መልስ ነው? ወይስ ሁሉም መልስ አይደለም?

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆች ላይ ቁጣውን እንዲያፈስስ የሚያደር ጉት ከጎረቤት ሐገሮች (ከአሕዛብ) የሚኮር ጇቸው የተለያዩ ጣዖታት ነበሩ፦ በኣል፣ አሽታሮት፣ ቤል፣ ናባው፣ ወዘተ...። የአዲስ ኪዳኗ ዋነኛ ጣዖት ዓለም ነች። ዓለም ስንል ጸረ እግዚአብሔር የሆነውን ማንኛውንም ነገር፣ አመለካከትና በክፉው ተጽእኖ ሥር ያለውን ክፉ ሲስተም ሁሉ ማለታችን ነው። ዓለም ማለት ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የሚያቀዘቅዝ ማንኛውም ነገር ነው። ለእግዚአ ብሔር ያለንን ፍቅር ነገሮች እንዲያቀዘቅዙ ከፈቀድን ዓለማውያን ‹‹ክርስቲያኖች›› እንባላ ለን፤ ዓለማዊም ክርስቲያንም መሆን የሚቻል ከሆነ ማለት ነው።

የፍቅር ደቀ መዝሙር በመባል የሚታወቀው ሐዋርያው ዮሐንስ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በዓለም ፍቅር እንዳንለውጠው አበክሮ ያሳስበናል፦ ‹‹ዓለምንና በዓለም ያለውን ማንኛውንም ነገር

 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

አትውደዱ፤ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የዐይን አምሮትና የሥጋ ምኞት ስለ ገንዘብም መመካት ነው። ስለዚህ ማንም ዓለምን ቢወድ የአብ ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአ ብሔርን ፍቅር የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል›› (1ኛ ዮሐ 2፡ 15)። ሐዋርያው ያዕቆብም እጅግ አጠንክሮ ዓለማውያን ክርስቲያኖችን ይገሥጻል፦ ‹‹አመንዝሮች ሆይ ዓለምን መውደድ በእግዚአብሔር ዘንድ ጠብ እንደሆነ አታውቁምን። የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚወድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል›› (ያዕቆብ 4፡4)።

ዓለምን ስንወድ በሐዋርያው ዮሐንስ መልእክት መሠረት እግዚአብሔርን ልንወድ አንችልም። ምክንያቱም ሁለቱ መውደዶች በአንድ ላይ በአንድ ጊዜ ሊገኙ አይችሉም። ልክ ብርሃንና ጨለማ ባንድ ጊዜ ባንድነት እንደማይገኝ ሁሉ። የዓለም ፍቅር ወደ ልባችን ሲገባ ወዲያውኑ በዚያች ቅጽበት የእግዚአብ ሔር ፍቅር ከውስጣችን ይወጣል። የእግዚአ ብሔር ፍቅር በውስጣችን ከሌለ እግዚአብ ሔርን ማምለክ አንችልም። እናመልካለን ብንልም እንኳ ሜዳዊ፣ ውጫዊ ሥርዓት ብቻ ነው የሚሆነው። ሐዋርያው ያዕቆብ የዓለም ወዳጆችን አመንዝሮች ይላቸዋል። አመንዝራ ማለት ለሚስቱ ወይም ለባሏ ሊሰጥ/ልትሰጥ የሚገባውን/ የሚገባትን ፍቅር ለሌላ የሚሰጥ/ የምትሰጥ ማለት ነው። በኩር ልጁን የሰጠን እግዚአብሔር በኩር ፍቅራችንን እንድንሰጠው ይሻል። በሕይወታችን በኩራት ላደረግናቸው ነገሮች (ጣዖታት) ፍቅራችንን (የመውደድ ዐቅማችንን) ከሰጠን ቅዱሱን አምላክ እያመለክነው አይደለንም። አንድ ሰው ባንድ ጊዜ ነገሮችንና እግዚአብሔርን ሊያመ ልክ አይችልም። ምክንያቱም እግዚአብሔር በደባልነት መመለክ ስለማይሻ። እርሱ በሕይወታችን የመጀመሪያውን ስፍራ ካላገኘ ወይም አንደኛ ካልሆነ ከታች ያሉትን የትኞቹንም ደረጃዎች አይቀበልም። ምክንያ ቱም እግዚአብሔር በልቡ ውስጥ የመጀመሪያ ውን ስፍራ/ ደረጃ ተሰጥቶናልና።

**‹‹ልጆች ሆይ ራሳችሁን ከጣዖታት ጠብቁ›› (1ኛ ዮሐ 5፡21)፡**

## 1.6 ማጠቃለያ

አምልኮ በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሣ በዚህ አጭር ጽሑፍ መባል ያለበትን ነገር ሁሉ ማለት የማይሞከር ነው። ነገር ግን ከላይ ለመንደርደሪያ የቀረቡት ሐሳቦች ስለ አምልኮ ባለን መረዳት ላይ ጥቂት ግንዛቤ ይጨምራሉ። በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አምልኮ የሚለው ቃል ከዝማሬ ጋር ለዚያውም ፈጠን፣ ሞቅና ደመቅ ካለ ዝማሬ ጋር ብቻ እየ ተያያዘ መምጣቱ የአምልኮን ትርጉም በጣም ያጠበዋል። ቃሉ አምልኩ ሲል ሁል ጊዜ በሁሉም ቦታ በቅዱስ አምላክ ፊት እንዳላችሁ በማወቅና በመረዳት ኑሩ ማለቱ ነው። በኩር ፍቅራችሁን እግዚአብሔርን ለመውደድ/ ለማምለክ አውሉት ማለቱ ነው።

ዞሮ ዞሮ እግዚአብሔርን የምናመልከው አምልኳችን ለእግዚአብሔር አንዳች የሚጨምርለት ነገር ስላለ አይደለም። ፍቅራችንን/ አምልኳችንን ስላጣ የእግዚአብሔር ዙፋኑ አይነቃነቅም። ‹‹ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ...እኔ አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝ›› (ዘፀ 20፡3፣6) ሲልም የሚቀናው ለራሱ ብሎ ሳይሆን ስለ እኛ ብሎ ነው። አንድ መልካም አባት ለሚወደው ልጁ እንደሚቀና ዐይነት ቅናት ነው። ፍቅር የሆነው አምላካችን፣ ሕይወታችን ከእርሱ ውጭ ብትንትኑ እንደሚወጣ ያውቃል፣ ትርጉም እንደሌለው እርካታ እንደ ሌለው ያውቃል። ያለ እርሱ ምንም እንደማያምርብን፣ ምንም እንደማይሆንልን ያውቃል። ስለዚህ ነው የሚቀናው።

 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

አምልኮ በሆነ ቀን፣ በሆነ ሰዓት ተሰብስቦ ሥርዓት የመፈጸም ጉዳይ አይደለም። በዚህች ምድር እንኳን ትርጉም ያለው ሕይወት ለመኖር፣ አምልኮ ለሰው ልጅ የጎልውና ጉዳይ ነው። የአምልኮ ሕይወት ለአንድ አማኝ ልክ ለአንድ ዓሳ የባሕር ሕይወት እንደሆነው ነው። ዓሳ ከባሕር ከወጣ እንደሚሞት አማኝ ከአምልኮ ሕይወት ከወጣ መንፈሳዊ ሞት ይሞታል።

**...**የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ።
እኔና ቤቴ ግን
እግዚአብሔርን እናመልካለን።
(ኢያሱ 24፡ 15)

# ክፍል ሁለት

## II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ/ ክርስቲያናዊ ዝማሬ

# መጽሐፍ ቅዱሳዊ / ክርስቲያናዊ ዝማሬ ምንድነው?

## 2.1 አጭር የዝማሬ ብያኔ

መንፈሳዊ ወይም ክርስቲያናዊ ዝማሬ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ፣ በግጥምና በዜማ የሚቀርብ፣ በሙዚቃ መሣሪያዎች ሊታጀብ የሚችል ለእግዚአብሔር ክብርን፣ ለአማኞች መታነጽን፣ በውጭ ላሉት ድነትን ሊያመጣ የሚችል መንፈሳዊ ስጦታ ነው።

መዝሙር መቼ ተጀመረ? የሚለውን በትክክል ለመመለስ አዳጋች ቢሆንም ዓለማት ከመፈጠራቸው በፊት፣ በሰማይ በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ዝማሬ ለእግዚአብሔር ይዘመር ነበር። እግዚአብሔር ዓለማትን ሲፈጥር ምናልባትም ‹‹ሥራህ ድንቅ ነው›› እያሉ በሚዘምሩ መላእክት ታጅቦ ነበር (ኢዮብ 37፡4-7)። በአሁኑ ሰዓት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን ተነጥቀን በዚያ የሚደረገውን ለማየት ቢፈቀድልን፣ በቃላት ሊገለጥ የማይችል፣ ከቶ ተደምጦ የማይታወቅ፣ ማንኛውም ምድራዊ የሙዚቃ ጠቢብ ሊያቀናብረው የማይችል ድንቅ ዝማሬ ያለማቋረጥ ለእግዚአብሔር ይቀርብለታል። ይህን ዝማሬ የሚያቀርቡ ቅዱሳን መላእክት፣ ቅዱሳን ሰዎችና ቅዱሳን ፍጥረታት ናቸው (ኢሳ 6፡1፤ ራእይ 4፡8፣11፣ 5፡9፣12፣13)።

## 2.2 ሙዚቃ ከውድቀት በኋላ

ሉሲፈር በእግዚአብሔር መንግሥትና በሥርዓቱ ላይ አምፆ ከሰማይ ከመጣሉ በፊት የሰማይ አምልኮ መሪ ነበር (ኢሳ 14፤ ሕዝ 28)። ከሰማይ ከተጣለበት ጊዜ አንሥቶ እስከዚህች ሰዓት ድረስ ሙዚቃ (ርኩስ ሙዚቃ) በዓለም ላይ፣ በተለይ ያለ ክርስቶስ በሆኑት ዐመፅን፣ ርኩሰትን፣ የከባድ ዕጾች ሱሰኝነትን፣ ክህደትን፣ ራስን በራስ ማጥፋትን የሚያስፋፋበት ትልቁ መሣሪያው ነው።

ዛሬ ሰይጣን የብዙ ሰዎችን ጊዜ፣ ጉልበት፣ ገንዘብ፣ ፍቅር፣ ተቆጣጥሮ በመያዝ ስለ ዘላለምና ዘላለማዊ ፋይዳ ስላላቸው ነገሮች ቆም ብለው እንዳያስቡ ነገር ግን በዓለማዊው፣ በጊዜያዊው፣ በአላፊውና በጠፊው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ እያደረጋቸው የሚገኘው በዘፈን፣ በርኩስ ፊልሞችና በሌሎች ርኩስ መዝናኛዎች አማካይነት ነው። ሰዎችን ለዘላለማዊ ጥፋት የማዘጋጀትና የማዝናኃት ተግባር ወይም ሙያ ላይ ለተሰማሩት አገልጋዮቹ (entertainers) ሉሲፈር እጅግ ብዙ ብር፣ እጅግ ብዙ ክብር፣ ቁሣቁስና ዝና ይሰጣቸዋል። ‹‹ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል›› (ማቴ 16፡26)? ምንም። ለዚህ ነው የኢንተርቴይመንት ኢንደስትሪ የሚባለው ባለብዙ ቢሊየን ኢንቬስትመንት የሆነው። አንድ ሰው እንዳለው ሰይጣን ውሸትን ፋይናንስ ያደርጋልና።

## 2.3 የዝማሬ ኪነ ጥበባዊነት

ከላይ በ2.1 በተመለከትነው የዝማሬ ብያኔ/ ትርጉም ውስጥ መፈልቀቅ ያለባቸው ብዙ አላባውያን አሉ። ነገር ግን ሁሉንም በዚህ ቦታ በስፋት ለመዳሰስ ስለማንችል ጠቀስ አድርገን የምናልፋቸው አሉ፤ ደግሞም በመጠኑ ዘርዘር አድርገን የምናያቸው አሉ። የዝማሬን ኪነ ጥበባዊ ጎን ለምሳሌ ሙዚቃውን፣ ዜማውን፣ ሥነ ግጥሙን በሚመለከት ጠቅሰን ብቻ እናልፋለን። ነገር ግን ‹‹በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ፣ ለእግዚአብ ሔር ክብርን፣ ለአማኞች መታነጽን፣ ለኮበለሉት መመለስን፣ ላልዳኑት

ድነትን›› የሚለውን የብያኔ ክፍል የሕያው ዝማሬ ምንጮችና የዝማሬያችን ተደራስያን ወይም ታዳሚዎች በሚሉት ንዑሳን ርእሶች ውስጥ በአንፃራዊነት ሰፋ አድርገን እናያለን። ‹‹በግጥምና በዜማ የሚቀርብ፣ በሙዚቃ መሣሪያዎች ሊታጀብ የሚችል›› የሚል ሐረግ አለው ብያኔው። ስለ ግጥምና ስለ ዜማ ስለ ሙዚቃ መሣሪያዎች እጀባ በጥቂቱ ብቻ እናነሳለን።

ዝማሬ ሰማያዊ ወይም መንፈሳዊ ነው ስንል ዝም ብሎ በላያችን ላይ ይወድቅብናል ማለት አይደለም። ወይም ደግሞ በፍጥሞ ደሴት ዮሐንስ ራእይ በተቀበለት መንገድ ‹‹እንዲህ ብለህ ጻፍ›› ተብሎ ‹‹በዲክቴሽን›› ይነገረናል ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ ይህ ማለት ጌታ በዚህ መንገድ መናገር አይችልም ማለት አይደለም። እርሱ ሉዓላዊ አምላክ በመሆኑ በፈቀደው መንገድ መናገር ይችላል። ነገር ግን ሥነ ግጥሙንና ዜማውንና ሙዚቃውን በሚመለከት የሰው ጉልህ ድርሻ አለበት። የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ አለ፤ የእኛም ድርሻ አለ። አንዳንድ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ የመቀስቀስ ድርሻ 10 ከመቶ የእኛ ጥረትና ሥራ 90 ከመቶ ነው ‹‹10% inspiration 90% persipiration›› ይላሉ›› እንዲህ አድርጎ በእርግጠኝነት በአሃዝ ማስቀመጡ አስቸጋሪ ቢሆንም አባባሉ እውነትነት አለው። መንፈስ ቅዱስ እኛን ወክሎ እኛ መሥራት የምንችለውን ነገር አይሠራልንም።

አንዳንድ ዘማሪዎች ዝማሬያቸውን መንፈስ ቅዱስ የሰጠኝ ነውና ማንም ሊያርመው አይገባም ሲሉ የሚሳሳቱት ለዚህ ነው። መንፈስ ቅዱስ የሰጠኝ ዝማሬ ነውና ማንም መዝሙሬን ሊሄስም ሆነ አስተያየት ሊሰጥበት አይችልም የሚሉ ዘማሪያን ይህን ዐቋማቸውን ካላለሳለሱ በስተቀር በዝማሬያቸው ሊከሰት ለሚችለው ሥነ መለኮታዊና ሥነ ጽሑፋዊ ግድፈት ኃላፊነቱን ለመውሰድ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

## 2.2.1 የዝማሬ መልእክት

ማንኛውም ክርስቲያናዊ አገልጋይ በአንድም በሌላም መንገድ የሕያው እግዚአብሔር መልእክተኛ ነው። አገልግሎትም በዋናነት የእግዚአብሔር መልእክተኛ መሆንና ይህን መልእክት ማድረስ የሚያስከፍለውን ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆን ማለት ነው። ‹‹ከእግዚአብሔር የተላከ ስሙ ዮሐንስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ። …እርሱ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ…›› (ዮሐ 1፡6)። ዘማሪም ከእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር የተላከ ከሆነ የእግዚአብሔር ምስክር፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው፡- አማኞችን የማነጽ፣ ደፋሮችን የመገሠጽ፣ ኮብላዮችን የመመለስ፣ በውጭ ያሉትን ኑ ግቡ የማለት ነው መልእክቱ፤ እግዚአብሔርን በዝማሬዎቹ ማወደስና ማመስገን እንዳለ ሆኖ።

የዝማሬ መልእክት በዋናነት ከቃሉ ውስጥ የሚወጣና በመንፈስ ቅዱስ አብረሆት የሚገኝ ነው። ዘማሪ የማያመቻምች ቆራጥና ስለ ወንጌል ሁሉን ለመሆን የተዘጋጀ መሆን ይኖርበታል። ስለ ዝማሬ መልእክት ወይም ይዘት ስለ ዝማሬ ተደራስያን ስናነሣ በሚገባ ትንተና እንሰጣለን። ለጊዜው ዝማሬ መልእክት እንዳለውና ዘማሪም መልእክተኛ እንደ ሆነ ጠቅሰን በእዚሁ እናብቃ።

## 2.2.2 የዝማሬ ሥነ ጽሑፍ

መልእክት በብዙ መንገዶች ይተላለፋል። አንደኛው መንገድ ሥነ ጽሑፍ ነው። ዝማሬ ደግሞ በግጥም የሚተላለፍ መልእክት አለው። የዝማሬው መልእክት በጥሩ ሁኔታ ጎልቶ የሚወጣው መዝሙሩን የሚጽፈው ሰው የሥነ ግጥም ሕግጋትን ጠብቆ፣ ሥነ ግጥም የሚጠቀምባቸውን ዘይቤዎች ምንነት ተረድቶ የመዝሙሩን ግጥም የጻፈ እንደሆን ነው። ይኼ በጣም ሰፊ ርእሰ ጉዳይ በመሆኑ እዚህ ቦታ በዝርዝር ለማንሣት አይሞከርም። ሆኖም በብያኔ መልክ ስለ ሥነ ግጥምና የሥነ ግጥም ዐበይት አላባውያን ጥቂት ብዬ አልፋለሁ።

 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

## ሀ. ሥነ ግጥም ምንድነው?

ሥነ ግጥም አንድን ነገር ወይም ድርጊት አድምቆና አጉልቶ የማሳየት፣ ሐሳብን አክርሮና አግዝፎ የማቅረብ ችሎታ ያለው፣ በጥቂት ምርጥ ቃላት ብዙ ነገሮችን አምቆ የሚይዝና በሙዚቃዊ ቃናው የስሜት ሕዋሳትን በቶሎ የሚነካ፣ ለስሜት ቅርብነት ያለው ኪነ ጥበብ ነው።

ዘሪሁን አስፋው

ሥነ ግጥም በአጅጉ ቁጥብነትና እምቅነት ያለው፣ በጥቂት ቃላት ብዙ ማለት የሚችል የሥነ ጽሑፍ ቅርፅ ነው። ከሌሎች የላቀ ከፍተኛ ኃይል ያለው ቋንቋ ነው።...ሥነ ግጥም ብርሃንና ሙቀት የሚያፈልቅ የሚንቦገቦግ ቋንቋ ነው።

ሎረንስ ፐርኒ

እነዚህ ብያኔዎች ስለ መዝሙር ግጥም ሳይሆን ስለ ማንኛውም ግጥም የሚናገሩ ቢሆንም መርሆዎቹ ግን ለመዝሙር ግጥምም ይሠራሉ። አንድን ሐሳብ እንኳንስ በግጥም ይቅርና በስድ (በዝርዉ) እንኳን ጥሩ አድርጎ ለሌሎች ማስተላለፍ ሁሉም ሰው የሚካንበት ሙያ አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ተሰጥዖው ያስፈልጋል፤ ተሰጥዖው ደግሞ በትምሕርት መዳበሩ የበለጠ ጠቀሜታ አለው።

አብዛኛዎቹ ዘማሪዎች ምናልባት በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ከሚገኘው የሥነ ጽሑፍ እንዲሁም የሥነ ግጥም አጠር ያለ የመግቢያ ትምህርት በስተቀር ከዚያ ያለፈ የሥነ ግጥም ትምህርት የቀሰሙ አይመስለኝም። ይህ ግን ደካማ የመዝሙር ግጥም ለመጻፍ በምክንያትነት ሊቀርብ አይችልም። ታዲያ ምን ይደረግ?

መዝሙር የሚጽፉ ሁሉ በተቻለ መጠን ስለ ግጥም ሰፋ አድርገው የሚያስተምሩ መጻሕፍትን ማንበብ፣ እንዲሁም ጥሩ የግጥም መጻሕፍትን ማንበብ፣ እንዲሁም ስለ ሥነ ግጥም ትምህርት የሚሰጥባቸውን ሴሚናሮች ማዘጋጀት/መካፈል የግጥም ችሎታን ለማሻሻል በጣም ይረዳል።

## ለ. የሥነ ግጥም አላባዊያን

ለምሳሌ መሠረታዊ ከሆኑት የሥነ ግጥም አላባዊያን መካከል ቤት መምታት፣ ቀለም፣ ምት፣ ሆሄ፣ ምጣኔ፣ ሀረግ፣ ስንኝ፣ እስታንዛ...የሚባሉት ይገኛሉ። እነዚህ ግጥምን ግጥም የሚያደርገውን ሙዚቃዊ ባሕርይውን እንዲጠብቅ ያደርጋሉ። አንድ ግጥም ቤት መታ የሚባለው በየስንኙ መጨረሻ በተመሳሳይ ሆሄ ብቻ ሳይሆን በዋናነት በተመሳሳይ ድምፅ ሲጨርስ ነው።

ሰማያት አድምጡ ምድርም ይህን ትስማ
አንድ ልጁን ሰጠን አምላክ ሳያቅማማ
ዘላለማዊው ቃል ሥጋ ሆኖ መጣ
አብን አየን በእርሱ ከምድር ሳንወጣ።

አንድ የግጥም መስመር ስንኝ ይባላል። ከላይ የተጠቀሰው የመዝሙር እስታንዛ የመጀመሪያ ስንኝ ‹‹ሰማያት አድምጡ ምድርም ይህን ትስማ›› የሚለው ነው። ይህ ስንኝ ሁለት ሐረጎች አሉት። ሐረግ የሚባለው የስንኝ እኩሌታ ወይም አንድ ስንኝ ሲነበብ ቆም ተብሎ ትንፋሽ የሚወሰድበት የመጀመሪያ ማረፊያ ነው። ከላይ የተጠቀሰው ባለ አራት ስንኝ ግጥም ስምንት ሐረጎች አሉት፡-

በስንኝ ሁለት ሐረጎች ማለት ነው። የመጀመሪያው ስንኝ ሁለት ሐረጎች የሚከተሉት ናቸው ‹‹ሰማያት አድምጡ›› እና ‹‹ምድርም ይህን ትስማ›› የሚሉት። አንድ ንዑስ መልእክት የሚያስተላልፉ የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ስንኞች አንድ አንጓ ወይም እስታንዛ ይፈጥራሉ። ከላይ በተጠቀሰው አንድ የመዝሙር እስታንዛ የሚገኙት አራት ስንኞች እያንዳንዳቸው ‹‹ማ›› በሚለው ሆሄና ድምፅ ይጨርሳሉ። በዚህ ጊዜ ቤት ይመታሉ ይባላሉ።

## ሐ. ዘይቤዎች

የግጥም ቁጥብነት፣ ውበት፣ ለዛና ጉልበታምነት ባብዛኛው በገጣሚው ዘይቤዎችን በጥበብ የመጠቀም ችሎታ ላይ የተመሠረተ ነው። ሥነ ግጥምን ሥነ ግጥም የሚያደርገው ዘይቤ ነው ብንል ከእውነት ብዙ አልራቅንም። ዘይቤ ምንድነው? አንድን ቃል በተለምዶ ከሚሰጠው ፍቺና አገባብ የተለየ ትርጉምና ፍቺ እንዲሰጥ አድርጎ መጠቀም ነው። የእያንዳንዱ ቋንቋ ተናጋሪ እያንዳንዱ ሰው በዕለት ተዕለት ሕይወቱ በጣም በተደጋጋሚ ዘይቤዎችን ይጠቀማል፤ ዘይቤ ምን እንደሆነ ባያውቅም። ይሁን እንጂ የዘይቤን ምንነት ዐውቆ መጠቀምና ሳያውቁ መጠቀም ትልቅ ልዩነት አለው። ለምሳሌ በዕለት ተዕለት ንግግራችን ብዙ ሳናስብ ዘይቤዎችን እንጠቀማለን አንዳንዶቹ የታኘኩና ለዛቸው ያለቀ፣ ብዙ ማሰብ የማይጠይቁ ቢሆኑም። ለምሳሌ ‹‹ዝናቡ ደበደበኝ›› ስንል ዘይቤ እየተጠቀምን ነው፤ የታኘከም ቢሆን። ዝናቡን ዱላ ይዞ ከሚደባደብ ሰው ጋር እያነጻጸርን ስለሆነ። ይኼ ዘይቤ ለዋጭ ዘይቤ ይባላል፣ ትንሽ ገለጻ ቢጨመርበት ምናልባት ሰውኛ ዘይቤም ሊሆን ይችል ነበር። ‹‹ፀሓይ አቃጠለኝ›› ስንልም ለዋጭ ዘይቤ እየተጠቀምን ነው። ‹‹ፀሓዩ እንደ እሳት አቃጠለኝ›› ካልን ግን አነጻጻሪ ዘይቤ ይባላል፦ የፀሓይዋን ማቃጠል ከእሳት ማቃጠል ጋር በማነጻጸር አጉልቶ ስለሚያሳየን።

መጽሐፍ ቅዱሳችን በዘይቤ የተንቆጠቆጠ መጽሐፍ ነው። በዚያ የሚገኙትን ዘይቤዎች ለይተን ለማወቅ፣ ለማድነቅና ለመጠቀም እንድንችል ዐበይት የሆኑ ዘይቤዎችን ብያኔዎች ቀጥሎ እንመለከታለን።

### 1. አነጻጻሪ ዘይቤ

በሁለት የማይመሳሰሉ ነገሮች መካከል አንድ ተመሳሳይ ነገር ፈልጎ የሚያመሳስል የዘይቤ ዐይነት አነጻጻሪ ዘይቤ ይባላል። አነጻጻሪ ዘይቤ አንድን የማይታወቅ፣ እንግዳ ወይም ረቂቅ ነገር ተዘውታሪ፣ ቅርብና የሚታወቅ አካላዊ ነገር ወይም ባሕርይ፣ ድርጊት ወይም ሁኔታ አማካይነት ያጎላል።

ለምሳሌ ዳዊት የክርስቲያናዊ ኅብረትን በረከትና ውበት ለመግለጽ አነጻጻሪ ዘይቤን ይጠቀማል፦

1 ወንድሞች ተስማምተው በአንድነት ሲኖሩ፣
  እንዴት መልካም ነው! ምንኛስ ደስ
    ያሰኛል!
2 በራስ ላይ ፈስሶ፣ እስከ ጢም  እንደሚዘ
      ልቅ፣
እስከ አሮን ጢም እንደሚወርድ፣
እስከ ልብሱም አንገትጌ እንደሚደርስ
      ውድ ሽቱ ነው።
3 ደግሞም በጽዮን ተራራ ላይ እንደሚወርድ
እንደሚወርድ፣ እንደ አርሞንዔም ጠል ነው፤
በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን፣ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዟልና።

(መዝሙር 133)

በዚህ ምዕራፍ ቁጥር 1 እና 2 ላይ ተስማምተው በአንድነት የሚኖሩ ወንድሞችና እህቶች የሚፈጥሩትን መንፈሳዊ ስምረት በአሮን ራስ ላይ ፈስሶ እስከ ልብሱ አንገትጌ (ኮሌታ) እንደሚዘልቅ በእግዚአብሔር ልዩ ትእዛዝ ከተቀመመ እጅግ የከበረ ሽቱ ጋር ያነጻጽረዋል። በመቀጠል በመጨረሻውና 3ኛው ቁጥር ላይ ደግሞ ይኼንኑ የቅዱሳን ኅብረት በጽዮን ተራራ ላይ ከሚወርደው አርሞንዔም ጠል ጋር ያነጻጽረዋል። ከላይ በተመለከትናቸው ሁለት አነጻጻሪ ዘይቤዎች ልብ ማለት የሚገባን ‹‹....እንደሚፈስ ሽቱ ነው›› ቁጥር 2ለ እና ‹‹እንደ አርሞንዔም ጠል ነው›› ቁጥር 3ለን ነው። እንደ፣ ይመስላል፣ ከ፣ ወዘተ  አነጻጻሪ ዘይቤን ለይተን እንድናወቅ የሚረዱን (አንጻሪ) መስተዋድዶች ናቸው።

ሌሎች አነጻጻሪ ዘይቤዎችን እንመልከት፦

‹‹ሚስትህ በቤትህ ውስጥ እንደሚያፈራ ወይን ናት›› (መዝ 128፡ 3)።
‹‹ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው›› (መዝ 128፡
‹‹ሳኦልና ዮናታን...ከንስርም ይልቅ ፈጣኖች፣ ከአንበሳም ይልቅ ብርቱዎች ነበሩ››
(2ኛ ሳሙ 1፡ 23)።

በአነጻጻሪ ዘይቤ የተጻፈ አንድ የቆየ የሙሉ ወንጌል ሀ መዘምራንን ዝማሬ ጠቅሼ ወደሚቀጥለው ዘይቤ እንሸጋገራለን፦

እንደ ንጹሕ የማር ወለላ
እንደ ጣፋጭ የወይን ዘለላ
እንደ ክቡር የዕንቁ ፍንካች
ፍቅሩ አይደለም ታካች።

በዚህ ቦታ ዘማሪዎቹ በተለይም የዚህ ዝማሬ ደራሲ በጣም አስደናቂ የሆነ የዘይቤ አጠቃቀምና የቃላት አመራረጥ ሲጠቀም እንመለከታለን::

እጅግ ረቂቅ የሆነውን ፍቅር፣ ለዚያውም በቃላት ሊገለጥ የማይችለውን የጌታን ፍቅር ለመግለጥ ንጹሕ ከሆኑ ነገሮች የማር ወለላን፣ ጣፋጭ ከሆኑ ነገሮች መካከል ደግሞ የወይን ዘለላን ከከበሩ ድንጋዮች ደግሞ የዕንቁ ፍንካችን በመምረጥ እንደ በሚል መስተዋድድ ያነጻጽራቸዋል። ረቂቁን አይታዬውን፣ አይቀመሴውን፣ አይዳሰሴውን ፍቅር፣ ከፍቅርም የክርስቶስን ፍቅር፣ በጳውሎስ አገላለጽ ‹‹ስፋቱና ርዝመቱ፣ ከፍታውና ጥልቅነቱ ከመታወቅ የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር›› () በቃላት ለመግለጽ ያደረገው ሙከራ እጅግ የሚደነቅ ነው። ይህን መንፈስ ቅዱስ በውስጡ ያስቀመጠውን መልእክት፣ እግዚአብሔር የሰጠውን አእምሮ በመጠቀም፣ ጊዜ ወስዶ በተመጠኑና በተዋቡ ቃላት የፎቶግራፍን ያህል አግዝፎ በዓይነ ሕሊናችን የሳለልንን፣ የቀመስነው እስኪመስለን በቃላት ከሽኖ ያቋደሰንን ወንድም ወይም እህት ጌታ ይባርካቸው። ንጹሑ የማር ወለላና ጣፋጩ የወይን ዘለላ ምራቃችንን ያስውጠናል። የዕንቁው ፍንካች ሲንቦገቦግ በእዝነ ሕሊናችን ግዘፍ ነሥቶ ይታየናል። ውብ ቅኔ! ውብ (አነጻጻሪ) ዘይቤ! ውብ ዝማሬ!

2. ለዋጭ ዘይቤ
ሁለት የተለያዩ ነገሮችን ለማነጻጸር ማንጸሪ ያው ተነጻጻሪውን ተክቶ እንዲገባ በማድረግ የሚፈጠር ዘይቤ ነው::)

## 2.3 መዝሙር ከዬት ይመጣል? የሕያው ዝማሬ ምንጮች

ብዙ መዘምራን ደጋግመው የሚጠይቁት አንድ ጥያቄ አለ። ይህም ‹‹ጌታን እያከበረ፣ አማኞችን እያጽናና፣ ዓለምን በወንጌል እየማረከ ጉልበታምና ተወዳጅ ሆኖ ለዓመታት የሚቆይ ዘመን-ዘለቅ ዝማሬ እንዴት መጻፍ/ መድረስ ይቻላል?›› የሚል ነው። ሕያው የሆነ፣ ዘመን ዘለቅ፣ ክርስቲያናዊ/ መንፈሳዊ ዝማሬ መጻፍ በመጀመሪያ ደረጃ ሜዳዊ፣ ውጫዊ ጥበቦችን በማጥናት፣ በትምህርትና በሥልጠና የሚቀሰም፣ ጥሩ የኪነ ጥበብ ሰው በመሆን ብቻ የሚመጣ ጉዳይ አይደለም። ዓለማዊው ኪነ ጥበብ የሚጠይቀው ኪነ ጥበባዊ ተሰጥዖን ብቻ ነው። የሰው ሕይወትና ኑሮ ከግምት ውስጥ አይገባም። ወደ መንፈሳዊ አገልግሎት ስንመጣ ግን ዋናው የዘማሪው፣ የሰባኪው፣ የአርቲስቱ መንፈሳዊነት ነው። መንፈሳዊ አገልግሎት ከመንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ ይወጣልና። ስለዚህም ሕያው፣ ክርስቲያናዊ ዝማሬ መጻፍ ከሙዚቃ ችሎታ፣ ከግጥም ችሎታ፣ ከጥሩ ድምጻዊነት በላይ ነው።

በዋናነት ሦስት የሕያው ዝማሬ ምንጮች አሉ፡-እነዚህም ሕያው ቃሉ፣ ሕያው መንፈሱና የሕይወት ተሞክሮ ናቸው።

### 2.3.1 የመጀመሪያው ምንጭ ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ነው

ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስይስ 3፡16 ላይ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባቸሁ ካለ በኋላ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ ለጌታ ዘምሩ፣ እንዳችሁ ለሌላችሁ ዘምሩ ይላል። ሕያው ዝማሬ ከሕያው ምንጭ ይቀዳል። ሌላ ምንም ዐቋራጭ መንገድ የለም። እንዴት ነው ዝማሬዎቻችን በቃሉና በመንፈሱ የተሞሉ የምናደርጋቸው?

መጽሐፍ ቅዱሳችንን ገልጠን፣ ጥቅሶችን ገልብጠን፣ መዝሙር በመጻፍ ነውን? አይደለም። ዝማሬያችንን በቃሉ የምንሞላው በቅድሚያ እኛ በቃሉ ስንሞላ ብቻ ነው። እኛን የቀረጸን፣ የሠራን፣ የመከረን፣ ያጽናናን፣ የተዋሃደንን ቃል መንፈስ ቅዱስ ሲያቀብለንና ስንዘምረው ነው ዝማሬው ሕያው የሚሆነው። ቃሉን ስንሞላ ቃሉ በውስጣችን ብዙ ነገር ያደርጋል፡- መቆረጥ ያለበትን ይቆርጣል፣ መነቀል ያለበትን ይነቅላል፣ መፍረስ ያለበትን ያፈርሳል፣ መገንባት ያለበትን ይገነባል፣ ቃሉ ውሃ ነው ሕይወታችንን ያጥባል፣ ይቀደሳልም።

የብዙ ዘመናዊ ዝማሬዎች ዋና ችግር መልእክታቸው የተመሠረተው ሕያው በሆነው፣ በማይለወጠው፣ ዘላለማዊ ቃል ላይ ሳይሆን ባብዛኛው በዘማሪው ጊዜያዊ ስሜትና ምድራዊ በረከት ላይ ብቻ መሆኑ ነው። ‹‹...ይጨመርላችኋል›› የተባለውን ቀዳሚ ያደረገ ‹‹አስቀድማችሁ...ፈልጉ›› የተባለውን ደግሞ ቸል ያለ ይህ የተዛባ ትኩረት ነው የብዙ ዝማሬዎችን ዕድሜ አጭር ያደረገው። እንግዲያውስ ዝማሬ ሙሉ መልእክት ማስተላለፍ እንዲችል ዘማሪው በቃሉ ሊሞላ የግድ ነው። የዚያን ጊዜ ብቻ ነው

በዝማሬው እግዚአብሔርን ማክበር፣ አማኞችን ማነጽ ማለትም ማስተማር፣ መገሠፅ፣ ማቅናት፣ ማበረታታትና በጽድቅ መንገድ መምከር የሚችለው (2ኛ ጢሞ 4፡2)።

## 2.3.2 ሁለተኛው ምንጭ ሕያው የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 5፡18 ላይ ‹‹መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ካለ በኋላ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊ ቅኔ ለጌታ ተቀኙ እርስ በርሳችሁ ተናነጹ ይላል። በመንፈሱ መሞላት በቃሉ ከመሞላት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ነው። የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ በአንድነት ይሠራሉ። ከላይ የጠቀስነው የጢሞቲዎስ መልእክት ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ…›› ይላል። የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ መለያየት እስከማይችሉ አብረው የሚሠሩ ናቸው። ጌታችንም ሲያስተምር ‹‹እኔ የምነግራችሁ ቃል መንፈስም ነው ሕይወትም ነው›› (ዮሐንስ 6፡ 63) አለ።

እነዚህ ሁለቱ ምንም መተኪያ የላቸውም። ምንም እንኳን የምናወራው ስለ ዝማሬ በመሆኑ የቃሉ ሙላትና የመንፈሱ ሙላት ለሕያው ዝማሬ አስፈላጊ ናቸው እንበል እንጂ የትኛውም ክርስቲያናዊ መንፈሳዊ አገልግሎት ያለ ቃሉና ያለ መንፈሱ ፈጽሞ ውጤታማ አገልግሎት ሊሆን አይችልም። ለዚህ ነው በዘካርያስ 4፡6 ላይ ‹‹በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም›› የሚለው። እንዲሁም ጌታችን ከማረጉ በፊት የመጨረሻው ተስፋና ትእዛዝ ‹‹እነሆም አባቴ የሰጠውን ተስፋ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ›› (ሉቃስ 24፡49) ያለው። ከትንሣኤው በኋላም ‹‹…መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ … እስከ ምድር ዳርቻም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ›› (ሥራ 1፡8) ካላቸው በኋላ ወዲያውኑ አረገ።

ሰዎች በቃሉ ሲሞሉ በመንፈሱም ይሞላሉ፤ በመንፈሱ ሲሞሉም መንፈስ ቅዱስ በከፍተኛ ሁኔታ ወደ ቃሉ ይመራቸዋል፣ ቃሉን ይገልጥላቸዋል፤ የቃሉን ረሓብ (እውነተኛ አፒታይት) ይሰጣቸዋል።

## 2.3.3 ሦስተኛው፣ የዘማሪው የሕይወት ተሞክሮ (life experience) ነው

መዝሙር 40፡1-2 ዳዊት ይህን ግልጽ ያደርጋል። በዚህ ቦታ ዘማሪው፣ ንጉሡና ነቢዩ ዳዊት ማንም ሊያወጣው በማይችል ረግረግ (መንፈሳዊ ችግር) ውስጥ እንደ ገባ ይነግረ ናል። ለረዥም ጊዜ እግዚአብሔርን ከዚህ ማጥ እንዲያወጣው ተማጸነው፤ እግዚአብሔ ርም ከረግረግ ማጥ አውጥቶ በዓለት ላይ እግሮቹን አቁሞ አጸናቸው፡- ወዲያው ‹‹አዲስ ዝማሬን ለአምላካችን የሚሆን ውዳሴ በአፌ ላይ አኖረ›› ይላል። እግዚአብሔር ከእንዴት ዐይነት ዐደጋ እንደ ታደገው እየመሰከረ በዝማሬ እግዚአብሔርን ሲያወድስ ብዙዎች ሰምተው ፈሩ! በእግዚአብሔር ታመኑ። እንዲህ ዐይነት ቅዱስ ፍርሃት የሚያመጣ ዝማሬ እንድንዘምር እግዚአብሔር ይርዳን።

ሁሉም አንጋፋ ሶሎ ዘማርያን በርካታ የሕይወት ተሞክሮ ዝማሬዎች አሏቸው። ሆኖም ደረጀ ከበደ በተለይ በዚህ ይታወቃል። መንፈሳዊ አድራሻውን ወይም እያለፈበት ያለውን ወይም ያለፈበትን የሕይወት ውጣ ውረድ የመግለጽ ዐቅማቸው ከፍተኛ በሆነ ቅኔና ዜማ በተከሸኑ ዝማሬዎቹ አቅርቦልናል። አንዱን ለአብነት ብንመለከት፡-

> ዞር ብዬ ሳየው ያሳለፍኩትን፣
> አባጣ ጎርባጣ ጉድጓድ ገደሉን
> ማመን ይሳነኛል ኃይል ከየት አገኘሁ



እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

ለካስ ኤልሻዳዩ ጠብቆኝ ኖሬያለሁ።

1. አጭር ጊዜ አይደለም ለረዥም ዘመናት
   በድካም በትግል ለአያሌ ዓመታት
   በመውደቅ መነሣት በውጊያ በጽናት
   እንደማያልፍ የለም አለፈ ያ እሳት።

2. የሕይወቴ ማብቂያ ዛሬ ነው ያልኩበት
   ዐይኖቼን ጨፍኜ ሞትን ያሰብኩበት
   ቀውጢው ሰዓት አልፎ ማየቴ ደንቆኛል
   ለካስ ጌታ ወዶ እጅ እግሬን ጠብቋል።

3. መራራ አይታኝክ የመከራ እንጀራ
   የብቸኝነት ቤት እኔው ከእኔ ጋራ
   እንቅልፌን አጥቼ ብዙ ሌሊት አልፏል
   ዛሬ ግን ታሪክ ነው ተረት ነው ይወራል።

ሌሎች ተመሳሳይ መልእክት ያላቸው የደረጀ መዝሙሮች መስቀሌ ብዙ ነው፣ ሽንጤን ገትሬያለሁ፣ ዮናስ እኔ ነኝ ወዘተ ... ናቸው።

በእርግጥ ሁሉም የሕይወት ተሞክሮዎቻችን ወደ ዝማሬነት ይለወጣሉ ማለት አይደ ለም። መንፈስ ቅዱስ ወደ ውስጣችን ሲያመጣቸው ግን ገና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ወደ ዝማሬ ተቀይረው እግዚአብሔርን ሊያከብሩ፣ አማኞችን ሊያንጹና በክርስቶስ ድነት ያላገኙትን ወደ ድነት ሊመሩ ይችላሉ።

### 2.3.4 የታላቁ ዘማሪ የዝማሬ ምንጮች

ዘመን አይሽሬ ዝማሬዎችን የጻፈው የታላቁ፣ ተወዳጅ ዘማሪ ተሞክሮ በ2ኛ ሳሙኤል 23፡1 እና 2 ላይ ይገኛል። ዳዊት የኑዛዜ የሚመስል የመጨረሻ ቃሉን ፈለጉን ለሚከተሉ ዘማሪዎች ይሰጣል፡- ‹‹የዳዊት የመጨረሻ ቃሉ›› ብሎ ነው የሚጀምረው። ምንድነው እርሱ የመጨረሻ ቃሉ? ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ተናገረ፣ ቃሉም በአንደበቴ ላይ ነበረ›› ይላል።

ጸሐፊው ዳዊትን ‹‹የእስራኤል ተወዳጁ ዘማሪ›› ይለዋል። የድሮው ትርጉም ‹‹መልካም ባለቅኔ የሆነ›› ይላል። ኪንግ ጀምስ ‹‹በያዕቆብ አምላክ የተቀባው ጣፋጭ መዝሙረኛ›› ይለዋል፡- ‹‹the anointed of the God of Jacob, and the sweet psalmist of Israel" ይለዋል። የዳዊት ተወዳጅ ዘማሪነት፣ ለትውልድ ሁሉ መልእክት ያላቸው፣ ትንቢታዊ ዝማሬዎችን የመጻፉ ምሥጢር በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መንፈስ መሞላቱ ወይም መቀባቱ (1ኛ ሳሙ 16፡ 13፣23) መሆኑን ነው ‹‹የዳዊት የመጨረሻ ቃል›› የተባለው። እውነተኛ፣ ሰማያዊ ዝማሬን ለመዘመር ለሚሹ ሁሉ የመጨረሻው ቃል በዚህ ዘመናዊ ትውልድም ያው ነው፣ ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት እንደነበረው ሁሉ ነው፡- በሕያው ቃሉና በሕያው መንፈሱ ሳንሞላ ሕያው ዝማሬ፣ ዘመን ዘለቅ ዝማሬ መዘመር የምንችልበት ዐቋራጭ መንገድ የለም።

የዳዊት የሕይወቱ ተሞክሮዎችም የዝማሬዎቹ ምንጭ እንደ ነበሩ ቀደም ብለን የጠቀስነው መዝሙር 40 አስረጅ ነው። በተጨማሪም በመጽሐፈ መዝሙር የሚገኙ አንዳንድ መዝሙሮቹ በምን ዐውድ

ውስጥ ሆኖ እንደ ዘመራቸው ይናገራሉ። ለምሳሌ ዝነኛውን የንስሓ ዝማሬ፣ መዝሙር 51ን የጻፈው ነቢዩ ናታን መጥቶ በእግዚአብሔር ቃል ከገሠጸው በኋላ ነው። የመዝሙር 51 ርእስ ይህንኑ የሚያስታውስ ነው፦ ‹‹ዳዊት ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ፣ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ የዳዊት መዝሙር›› ይላል። ሌሎችም የዝማሬውን ዐውድ የሚያመለክቱ ተመሳሳይ የተለያዩ ርእሶች ያሏቸው ዝማሬዎች አሉ። ‹‹አምላኬ፣ አምላኬ ወዳንተ እገሠግሳለሁ፤ ነፍሴ አንተን ተጠማች፣ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች..በምድረበዳ ኃይልህንና ክብርህን አይ ዘንድ›› (መዝ 63) ብሎ የዘመረው ከሳዖል ሸሽቶ በኤዶሚያስ ምድረ በዳ በነበረ ጊዜ ነው። እንግዲያውስ የሕይወት ተሞክሮ ከቃሉ ጋር ተሰናስሎ፣ በጥበብ በጥሩ ዝማሬ ከቀረበ ምስክርነቱን የሚሰሙ እግዚአብሔርን ‹‹ይፈሩማል፣ በእግዚአብሔርም ይታመናሉ›› (መዝ 40፡3)።

## 2.4 ዝማሬ ለማን? የዝማሬያችን ተደራስያን/ታዳሚዎች

ደብዳቤ ስንጽፍ ተቀባይ ደብዳቤው የሚመለከተው ሰው አለ። መጽሐፍ ብንጽፍ መጽሐፋችንን አንብበው ይጠቀማሉ የምንላቸውን ሰዎች ታሳቢ አድርገን ነው የምንጽ ፈው። ዝማሬ ስንጽፍም በዋናነት የዝማሬያችን ታዳሚዎች አራት ናቸው፦ የመጀመሪያ ውና ዋናው ታዳሚ እግዚአብሔር ነው፤ ቀጥሎ አማኞች ናቸው፣ ሦስተኞቹ ኩብላዮች/ **backsliders** ሲሆኑ ያላመኑ ሰዎች አራተኛ ናቸው።

### 2.4.1 እግዚአብሔር የመጀመሪያው ታዳሚ ነው

‹‹ዘምሩ ለአምላካችን ዘምሩ፣ ዘምሩ ለንጉሣችን ዘምሩ፣ እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና በማስተዋል ዘምሩ›› (መዝ 47፡7) ይላል። ስለዚህ በቀጥታም በተዘዋዋሪም መንገድ እግዚአብሔር የዝማሬያችን ዋና ባለቤት ነው ። በዝማሬዎቻችን እንወድሰዋለን፣ እናመሰግነዋለን፣ እናመልከዋለን። እንዲሁም ደግሞ በዝማሬዎቻችን ሕዝቡን እንመክራ ለን፣ እናጽናናለን፣ እናስተምራለን፣ እንገሥፃለን፣ እናንጻለን።

በቅድሚያ ለእግዚአብሔር የሚዘመሩ ዝማሬዎች ርእሰ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ እንመል ከት። ወደ እግዚአብሔር የውዳሴ፣ የምስጋና፣ የአምልኮ፣ የልመና፣ የምልጃ፣ ዝማሬዎ ችን እናቀርባለን።

#### 2.4.1.1 የውዳሴ/ የምስጋና ዝማሬዎች

የውዳሴ ዝማሬዎች በሁለት ነገሮች ላይ ያተኩራሉ፦ የእግዚአብሔር ማንነትና የእግዚአብሔር ሥራ።

#### ሀ) የእግዚአብሔር ማንነት/ የእግዚአብሔር ስሞች

የእግዚአብሔር ማንነት/ ስሞች ስንል ባሕርያቱን ማለታችን ነው። ለምሳሌ ከእግዚአብ ሔር ባሕርያት መካከል የአምላክነቱ ገላጮች ወይም ለሌሎች የማያካፍላቸው ባሕርያት አሉት። ከእነዚህም መካከል ሁሉን ቻይነቱ፣ ሁሉን ዐዋቂነቱ፣ ባንዴ በሁሉ ቦታ መገኘቱ፣ ዘላለማዊነቱ፣ አይለወጤነቱ፣ ታላቅነቱ፣ ከመታወቅ በላይ መሆኑ (transc -endnce) ይገኙበታል። በማንነቱ ላይ የሚያተኩሩ፣ እግዚአብሔርን ስለማንነቱ የሚያወ ድሱት ዝማሬዎች በጣም ጥሩ የሚባሉ ዝማሬዎች ናቸው። ለምሳሌ በመዝሙረ ዳዊት ስሙን ቀድሱ፣ ስሙን አውድሱ፣ ለስሙ ዘምሩ የሚሉ ትእዛዛትን እናገኛለን። ስለ ማንነቱ፣ ስለ ባሕርያቱ ዘምሩ ማለት ነው። ስለ ሰው የሚዘፈን ዘፈን ባብዛኛው የሚያተኩረው በሰውዬው ወይም በሴትየዋ ውጫዊ ውበት ላይ ነው። ለእግዚአብሔር ስንዘምር

 

እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነና አካላዊ ውበት ስሌለው ለእግዚአብሔር የምንዘምረው የቅድስናውን ውበት ነው፤ ባሕርያቱን ነው።

እግዚአብሔር በተወሰነ ደረጃ ሰዎች ሊካፈሏቸው የሚችሉ ሌሎች ባሕርያትም አሉት፦ ከእነዚህም መካከል ቅዱስነቱ፣ ይቅር ባይነቱ፣ መሓሪነቱ፣ ቸርነቱ፣ ታጋሽነቱ ወዘተ ናቸው።

መጋቢ ተስፋዬ ጋቢሶ ስለ ሁሉን ቻይነቱ እንዲህ ይላል፦

ከዐቅምህ በላይ ሆኖ የሚከብድህ
ለመፍታት ከቶ የሚያስቸግርህ
ምን ችግር አለ የሚያዳግትህ
ሁሉን ቻይ የሆንክ ኤል ሻዳይ አንተ ነህ።

እንዲሁም ስለ ሁሉን ዐዋቂነቱ የሚናገር ዝማሬ አለው
በከፍታ ስፍራ በሰማይ ያለኸው
ምንም አይሳንህ ሁሉን ቻይ የሆንከው
ልብን ኩላሊትን የምትመረምረው
ጌታ ሆይ ጓዳችንን አጽዳው አጥበህ አስተካክለው።

ሳሙኤል ተስፋ ሚካኤልም የእግዚአብሔርን ሁሉን ዐዋቂነት ከሚተርከው መዝሙር 139 እየጠቀሰ ‹‹መልካም ነው›› በሚለው መዝሙሩ ውስጥ
‹‹ሳልፈጠር ያልተፈጠሩ ቀኖቼን ያየህ›› እያለ ይዘምራል።

ሳሙኤል ተስፋ ሚካኤል ስለ እግዚአብሔር አልፋና ዖሜጋ መሆንም ይዘምራል፦
‹‹አልፋ ነህ ዖሜጋ፣ መጀመሪያ መጨረሻ››

ሳሙኤል ቦርሳሞ ‹‹ፍቅር ነው፣ እግዚአብሔር ፍቅር ነው›› በሚለው መዝሙሩ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር መሆን ይዘምራል፦
ኃጢአት አስሸፍቶት ጫካ የገባውን
ጸጋውን ተገፎ የተራቆተውን
ወዳለበት ሰፈር ፍቅር ፈጥኖ ደርሶ
ዳግም ያቆመዋል ሚቹን አሥነስቶ…

ጌታ ያውቃልና ብሩክታይትም ፍቅር ኢየሱስ ነው ፍቅር በሚለው ዝማሬያቸው የኢየሱስን ፍቅር መሆን የሚተርኩ የወንጌል ታሪኮችን እየጠቀሱ የሚዘምሩት ድንቅ ዝማሬ አላቸው።

አንድ የቆየ ዝማሬ በአንድ አዝማች ውስጥ በርካታ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ይዘረዝራል፦
አቤት እንዴት ታላቅ ነህ!
እንዴት ታማኝ ነህ!
እንዴት ፍጹም ነህ!
የዘላለም አምላክ፣ የማትለወጥ!
የፍቅር አምላክ ጸንተህ ትኖራለህ።

## ለ) የእግዚአብሔር ሥራ

ሌላው ዐቢይ የውዳሴያችን ርዕሰ ጉዳይ የእግዚአብሔር ሥራ ነው። የእግዚአብሔር ሥራ በዋናነት በሦስት ይከፈላል። እነዚህም የመፍጠር ሥራው፣ የማዳን ሥራውና የመግቦት ሥራው ናቸው።

### ሀ. የመፍጠር ሥራው/ ፈጣሪነቱ

እግዚአብሔርን ስለ ፈጣሪነቱ እናወድሰዋለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔርን ስለ ፈጣሪነቱ የሚያወድሱ ብዙ ዝማሬዎች አሉ። የእግዚአብሔር ፈጣሪነትና የፍጥረቱ ትንግርት/ ታምር የሰው አእምሮ ከሚረዳው በላይ ነው። ዳዊትም ‹‹የጣቶችህን ሥራ ሰማያትን ባየሁ ጊዜ፣ ጨረቃንና ክዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው?›› (መዝ 8፡3) ይላል። መዝሙር 148ም እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ፍጥረ ታት በሙሉ መላእክትን፣ ፀሓይ፣ ጨረቃና ክዋክብትን፣ውሆችን፣የባሕር የሰማይ ፍጥረታትን፣ተራሮችን፣ኮረብቶችን፣የዱር አራዊት፣የቤት እንስሳትን፣ ወጣት ወንዶችንና ወጣት ሴቶችን ወዘተ እየጠራ እግዚአብሔርን አመስግኑት ይላል። እንዲሁም በራእይ 4፡11 ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው ‹‹ጌታችንና አምላካችን ሆይ ክብርና ሞገስ፣ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል፤ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና፤ ስለ ፈቃድህም ተፈጥረዋልና፣ ሆነዋልምና›› እያሉ ይዘምራሉ። የእኛም ዝማሬዎች ጌታን ስለ ፈጣሪነቱ የሚያመሰግኑ ቢታከሉባቸው በጣም ጥሩ ነው።

ደረጀ ከበደ በፈጣሪና በተፈጥሮ ላይ የሚያተኩሩ ብዙ ዝማሬዎች አሉት፡- ባጋጣሚ አንድ ቀን፣ ድንቅ ሥራ፣ እንዴት ድንቅ አምላክ ነው፣ ዝንጀሮ አይደለሁም፣ እግዚአብ ሔር የታለ ለምን ትለኛለህ… ቀጥሎ አንዱን ብቻ እንጠቅሳለን፡-

1. ኮረብታውን ወጥቼ እሮይ አልኩኝ
   ድንቅ የሆኑ ፍጥረታትን እያየሁኝ
   ብቻዬን ነኝ ለማለት አልደፈርኩም
   በዙሪያዬ አጫዋች አላጣሁም።
   ድንቅ ሥራ የአምላክ ሥራ አይወራ /2x

2. ቀስ እያልኩኝ ቀጠልኩኝ እርምጃዬን
   አቤት ወፎች ከበውኛል ዙሪያዬን
   ልዩ ልዩ ቀለም ለብሰው ሲጫወቱ
   ደስ ያሰኛል ያምላክ ጥበብ መሠረቱ።

3. ሽው እያለ በሚያዝናናኝ ነፋስ ደግሞ
   ሲወዛወዝ የእፅዋት አንገት ዘሞ
   ባምላክ እጆች በተሠሩት ተደንቄ
   ተመለስኩኝ ወደ ቤቴ ብዙ ዐውቄ።

ሳሙኤል ተስፋ ሚካኤልም ‹‹በሥራው ያስደነቀኝ›› በሚለው መዝሙሩ ውስጥ እግዚአብሔርን ስለ ፈጣሪነቱ እያደነቀ ያወድሰዋል፡-

አእዋፋት በአየር ላይ በከፍታ ሲበሩ
ነፋሱ ሲነፍስበት ሲነዋወጥ ባሕሩ
ደመናው ሲጠቁር ዝናቡን ሲያወርደው

ክረምት አልፎ ሲቀየር ሲተካ ደግሞ በጋው
ሳመልከው ስለ ሥራው እያልከኝ ጎንበስ ቀና
ራሱን ሳየው ጨመረብኝ ተገረምኩኝ እንደ ገና
ሥራው እንዲህ ያማረለት እርሱማ እንዴት ውብ ነው
የኔ ብቻ አይበቃውም ፍጥረት አብሮኝ ያድንቀው።

ፓ/ር ዮሐንስ ግርማም፣

ሰማይን በስንዝር እንዲህ አንጣልለሃል
የትልቅነትህ ብዛት ከሰው ስሌት ያልፋል
አንተ የሠራኸው በስንዝር የለካኸው
ይህ ሰማይ ትልቅ ከተባለ ሠሪው ምን ትባላለህ?

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅም አቤቱ ጌታችን በሚለው ዝማሬው
ሚፍለቀለቀው ምንጭ ፍቅር ነህ ይልሃል
ለምለሙ ቡቃያ ምስጋና ይሰጥሃል
ሜዳና ተራራው ውቅያኖስ ባሕሩ
እግዚአብሔር ታላቅ ነው እያሉ ዘመሩ፣ ይላል።

ሁሉም ዘማሪዎች በፈጣሪና በፍጥረቱ ላይ ተመሥርተው የዘመሯቸውን ዝማሬዎች በሙሉ ለመመልከት ጊዜው አይበቃንምና በዚሁ ወደሚቀጥለው እንሻገር።

## ለ. የማዳን ሥራው/ አዳኝነቱ

እግዚአብሔር፣ ገና በሰው ልጅ ታሪክ መጀመሪያ ላይ፣ የሰይጣንን ሽንገላ ሰምቶ በኃጢአትና በሰይጣን ቁጥጥር ሥር የሆነውንና የሞት ፍርድ የተፈረደበትን አዳምን ወደ ራሱ ለመመለስ ሥራውን የጀመረው በዚያው በኤደን ገነት ነው። በእርግማኑ ውስጥ የተስፋ ቃል ነበር፦ ‹‹እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፣ አንተም ተረከዙን ትቀጠቅ ጣለህ›› (ዘፍ 3፡ 15)። ይህም ከሺህ ዓመታት በኋላ ተገልጦ በመስቀል ላይ የዲያብሎስን ጭንቅላት የቀጠቀጠውንና የጥልን ግድግዳ በማፍረስ ሞትንና እርግማንን በመሻር ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር ያስታረቀውን የኢየሱስን ሥራ ያመለክታል። እርቃናቸውን በነበሩ ጊዜ እግዚአብሔር እንስሳትን በመሠዋት ያለበሳቸው የቆዳ ልብስም በመስቀል ላይ እርቃኑን በመንጠልጠል የሰውን ልጆች እርቃን ሊሸፍን ስላለው ስለ ኢየሱስ የሚተርክ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ታሪክ ወይም ማዕከሉ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ሊሠራ ያለውና ከሠራም በኋላ የሠራው ሥራ ነው። ብሉይ ኪዳን ወደዚህ ሥራ በጥላነት ያመለክታል፤ አዲስ ኪዳን ደግሞ ይህን ሥራ ይተርካል።

በመሆኑም የክርስቲያናዊ ዝማሬም ሆነ የክርስቲያናዊ ስብከት ዐቢይ/ ዋና መልእክት እግዚአብሔር በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለሰው ልጆች ሁሉ የሠራው ሥራ መሆን አለበት። እንደ እውነቱ ከሆነ የምሥራቹም ይኸው ነው። በራእይ መጽሐፍ ያለውን አምልኮ ስንቃኝ የዝማሬያቸው ትኩረት በጉና የበጉ መታረድ፣ በበጉ መታረድ የተሠራው ሥራ ነው። የሚያስገርመው በዚህ ተደንቀው ከሚዘምሩት አብዛኞቻቹ በጉ ያልታረደላቸው መላእክትና ለአምልኮ የተፈጠሩ ልዩ ፍጥረታት መሆናቸው ነው።
‹‹ለወደደን ከኃጢአታችንም
በደሙ ላጠበን››

(ራእይ 1፡ 5፣6)፣

‹‹መጽሐፉን ልትወስድ፣
ማኅተሞቹንም ልትፈታ ይገባሃል፤
ምክንያቱም ታርደሃል፤
በደምህም ከነገድ ሁሉ፣
ከቋንቋ ሁሉ፣ ከወገን ሁሉ፣
ከሕዝብ ሁሉ ሰዎችን ዋጅተሃል።
ለአምላካችንም መንግሥትና ካህናት አድርሃቸዋል፤
እነርሱም በምድር ላይ ይነግሣሉ››
(ራእይ 5፡ 9፣10)።

‹‹የታረደው በግ ኃይልና ባለጠግነት፣
ጥበብና ብርታት፣ ክብርና ሞገስ፣
ምስጋናም ሊቀበል ይገባዋል››
(ራእይ 12፡5)::

በአንጋፋዎቹም በወጣቶቹም ዘማሪዎች እጅግ በጣም ብዙ ዝማሬዎች ስለ መስቀሉ፣ ስለ ሞቱና ትንሣኤው በጥቅሉ በእግዚአብሔር አዳኝነት ላይ ተዘምረዋል። በተለይ ቆየት ያሉ ዘማሪዎችና ዝማሬዎች በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስላደረገው አብዝተው ይዘምሩ ነበር። ይህ ማዕከላዊ የሆነ የአዲስ ኪዳን መልእክት ዘመን የማይሽረው ነው። ሁሌም አብዝተን ልንዘምረው ይገባናል።

አንጋፋው ዘማሪ አዲሱ ወርቁ የዘመራቸው በርካታ መዝሙሮች በክርስቶስ ሕማማትና በመስቀሉ ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ጥቂቶቹን ብንጠቅስ፦

ትውስ ሲለኝ የጌታዬ ፍቅር ያደረገልኝ በጎልጎታ
ኮብልላ ነበረች/ ደሙን ለእኔ አፍስሶ
የደሙ ፍሬ ነኝ

ተስፋዬ ጋቢሶም

በቀራንዮ መስቀል ላይ በደዌ የደቀቀው
ነፍሱን ስለ ኃጢአቴ መሥዋዕት ያደረገው
የሞትን ቀንበር ሰብሮ እኔኑ ሊያወጣ ነውአ
ማዳኑን ቀምሻለሁ ምን አለ ምመልሰው።

ደረጀ ከበደም

ጌታዬ አነባ ለእኔ አለቀሰ
ሙቱን ሊያድን ብሎ ደሙን አፈሰሰ
ኤሎሄ ኤሎሄ አለ ጮኸ ወዳባቱ
ጣሩ በርትቶበት ቢባዛ ጭንቀቱ
ምስጋና እልልታ
ይገባዋል ለእርሱ ለሞተልኝ ጌታ።

አስቴር ተፈራም

ደሙ እንደ ውሃ ደሙ እንደ ውሃ ፈሰሰ
የጌታ ጀርባ በጅራፍ ተገረፈ
እግሩ እስኪነቃ ተራራውን ነጎደ
እስከ ሞት ድረስ ጌታዬ እኔን ወደደ።

ተስፋዬ ጫላ ስለ ትንሣኤው ድንቅ ዝማሬ ዘምሯል፡-

ገናናው የእኛ ኢየሱስ አቻ አይገኝለት
እንደ ሞተ አልቀረም ከቶ አለ በሰማያት
ማን ይቃወመናል ዛሬስ በደሙ ዋጅቶናል
ትንሣኤውን ልናወራ በገና እንሥተናል
በገና እንሥተናል።

ዳንኤል አምደ ሚካኤልም ስለ ድነት ስነ መለኮት ጥልቅ ዝማሬ ዘምሯል፡-

አዳነኝ በጸጋው አመሰግናለሁ
ኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወቴ ጌታ ነው
አምላክ በምሕረቱ ባዘጋጀው መንገድ
በወንጌሉ እውነተ ሰጠኝ ዳግም ልደት
...የሰው እጅ የሌለበት የእኔ ብሎ ሚያኮራ
በማመን የሚገኝኝ ጽድቅ በመስቀሉ ሥራ።

በዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ ከሃያ አምስት ዓመታት በፊት የተዘመረው የዘላለም ሸማዬ የሚለው ዝማሬም በክርስቶስ የማዳን ሥራና የጸጋው ትሩፋት ላይ የሚያጠነጥን ነው፡-

የዘላለም ሸማዬ የሱስ የሱስ ክበር
ጽድቁ ነህ ቅድስናዬ የሱስ የሱስ ክበር
የመርገም ጨርቄን ጣልኩኝ የሱስ የሱስ ክበር
አንተን ለብሼ አማርኩኝ የሱስ የሱስ ክበር።

1. ጸጋዬን ገፎኝ ኃጢአቴ በፊትህ ቢታይ እርቃኔ
   በገዛ እጄ ጽድቄን ላቆም ቅጠል ማገልደም ለምኔ
   ባንተ በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ ድፍረት አገኘሁ
   የመርገም ጨርቄን ጣጥዬው ወደ ጸጋህ ዙፋን ሸሸሁ። 2x

ለጊዜው እነዚሁ ይበቁናል።

## የመግቦት ሥራው/ መጋቢነቱ

አንዳንድ ፈላስፎች እንደሚሉት እግዚአብሔር ፍጥረታትን ፈጥሮ ዞር ያለ አምላክ አይደለም። ይልቁን መላውን ፍጥረት የሚጠብቅ፣ የሚመግብ፣ የሚንከባከብ ቸር አምላክ ነው።

በብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እግዚአብሔር በአምሳሉ ለተፈጠረው ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእንስሳትና ለአራዊት ሁሉ የሚገደው አምላክ መሆኑ ተጽፏል። ጥቂቶቹን ብቻ ለአብነት እንመልከት፡-

በመጽሐፈ ኢዮብ 38፡39-41 ላይ እንዲህ ይላል፡-

ለአንበሳይቱ አድነህ ግዳይ ታመጣላታለህን?
የተራቡ የአንበሳ ግልገሎችን ታጠግባለህን?
እነርሱ በዋሻ ውስጥ ያደባሉ፤
በደን ውስጥም ይጋደማሉ።
ልጆቿ ወደ እግዚአብሔር ሲጮኹ፣
ምግብ አጥተው ሲንከራተቱ፣
ለቁራ መብልን የሚሰጥ ማን ነው?

በመዝሙር 103 ላይ በሚገኙት 35 ቁጥሮች ውስጥ የእግዚአብሔርን የፍጥረተ ዓለም መጋቢነት በዝርዝር ይናገራል። በዚሁ ምዕራፍ በ27ኛው ቁጥር ላይ መዝሙረኛው መጋቢነቱን እንደሚከተለው ባጭሩ ያስቀምጠዋል፡-

…ምግባቸውን በወቅቱ ትሰጣቸው ዘንድ
እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ።
…እጅህንም ስትዘረጋ በመልካም ነገር ይጠግባሉ።

የቀድሞው ትርጉም በጣም ጥሩ አድርጎ ያስቀምጠዋል፡-

አንተ እጅህን ትከፍታለህ፤
ሕይወት ላለውም ሁሉ
መልካምምን ነገር ታጠግባለህ (መዝ 104፡27፣28)።

እንዲሁም በመዝሙር 136፡25

ለፍጡር ሁሉ ምግብን የሚሰጥ
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።

ደግሞም

ለተበደሉት የሚፈርድ
ለተራቡት ምግብን የሚሰጥ
እግዚአብሔር እስረኞችን ከእስራት ያወጣል፤
እግዚአብሔር የዕውራንን ዐይን ያበራል፤
እግዚአብሔር የተዋረዱትን ከፍ ከፍ ያደርጋል፤
…ስደተኞችን ይጠብቃል፣
ድኻ ዐደኅችንና መበለቶችን ይደግፋል፤
የክፉዎችን መንገድ ግን ያጠፋል
(መዝሙር 146፡7-9)

‹‹ለእንስሳት ምግባቸውን፣
የቁራ ጫጩቶች ሲንጫጩ
የሚበሉትን ይሰጣቸዋል››
(መዝሙር 147፡9)

ወደ አዲስ ኪዳንም ስንመጣ ጌታችን ኢየሱስ በፍጥረተ ዓለሙ መጋቢ እንድንደገፍ እንጂ እንዳንጨነቅ ግሩም አድርጎ በጥበብ አስተምሮናል፡-

ስለዚህ እላችኋለሁ፣ ስለ ኑሯችሁ ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስእንለብሳለን? በማለት አትጨነቁ። ሕይወት ከምግብ ሰውነትስ ከልብስ አይበልጥምን? እስቲ የሰማይ ወፎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም፣ አያጭዱም፣ በጎተራም አያከማቹም፤ ይሁን እንጂ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል። እናንተ ከእነርሱ እጅግ አትበልጡምን? ...የሜዳ አበቦችን ተመልከቱ...

(ማቴዎስ 6፡25-27፣28)

ስለ እግዚአብሔር መጋቢነት ወይም መግቦት የሚናገሩ መዝሙሮች እጥረት አለብን ብዬ ለመናገር አልደፍርም። ቁጥራቸው ቀላል ያይደለ ዝማሬዎች ርእሰ ጉዳዮች መብል፣ መጠጥ፣ ልብስ፣ መጠለያ፣ ስኬት፣ ጤና፣ ቁሣቁስ፣ ድሎት ወዘተርፈ ነውና። ባይሆን ምክሬ ሚዛናዊ እናድርገው ነው። ስለ ማንነቱና ስለ አዳኝነቱም አብዝተን እንዘምር ዘንድ ይገባናል።

## 2.4.1.2 የጸሎት/ የልመና ዝማሬ

አማኞች ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ዝማሬ የውዳሴ ብቻ አይደለም። የልመና ዝማሬዎችም ለእግዚአብሔር ይቀርባሉ። የልመና ማለት የጸሎት ዝማሬዎች ማለት ነው። ልክ በንግግር ወይም ከአንደበታችን በምናወጣቸው ቃላት ወደ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እንደምናቀርብ ሁሉ በዝማሬም ወደ እግዚአብሔር ጸሎታችንን እናቀር ባለን። በብሉይ ኪዳን በነበረው የመገናኛ ድንኳን በሌዋውያን ይዘመሩ እንደ ነበር የሚታመኑት በመጽሐፈ መዝሙር የሚገኙት ብዙ ዝማሬዎች በልመና/ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር የቀረቡ ናቸው። ዛሬም በርካታ የጸሎት ዝማሬዎች ይዘመራሉ። ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጸሎት ዝማሬዎች ከምናሳትማቸው አልበሞች ውስጥም፣ ከመዝ ሙር ደብተሮቻችን ውስጥም ቁጥራቸው እየተመናመነ መጥቷል። ምክንያቱ ምናልባት የጸሎት/ የልመና ዝማሬዎችን ማቅረብ እምነት የማጣት ምልክት ተደርገው ስለሚወ ሰዱ ይሆን?

ቀጥሎ የልመና ዝማሬ ለአብነት እንውሰድ። ለምሳሌ ተስፋዬ ጋቢሶ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ብርታትና መነቃቃት ጌታን በጸሎት ዝማሬ ይለምነዋል፡-

1. አንድ ነገር ሽቼ ደጅ እጠናለሁኝ

   ፈቃድህ ከሆነ በዐይንህ ተመልከተኝ<br>
   ያቺን ብሩክ እጅህን ዘርጋልኝ።<br>
   ዕንባዬን አይተህ ጌታ<br>
   ለቅሶዬን ሰምተህ ጌታ<br>
   መሻቴን ስጠኝና<br>
   የሱስ ላመስግንህ

2. መራራነቴ ያብቃ፣ እሾህነቴም ያብቃ<br>
   መፈራረሴም ያብቃ ባንተ ጸጋ ልገንባ<br>
   ጎስቋላነቴን ጌታ ሆይ እንካ።

እንዲሁም ይኸው ዘማሪ ለአንደበቱ መታረም በዝማሬ እግዚአብሔርን ይለምናል፡-

አንደበቴን አርም አንደበቴን<br>
እንደበቴን አርም።

### 2.4.1.3 የምልጃ ዝማሬ

የምልጃ ዝማሬዎች ለሌሎች ሰዎች ወይም ለሐገርም የሚዘመር ሊሆን ይችላል። አሁንም ተስፋዬን ብንጠቅስ ለኮበለሉት በዝማሬ ይማልዳል፦

የባዘነውን ፈላጊ አምላክ የምሕረት አምባ
ለጠፉትም የምታነባ
ከሕይወት ወደ ሞት
ከሞት ወደ ጭንቀት
የሄደውን መልስ ባክህ ጌታ
ወደ መንጋህ በረት።

የጅማ መዘምራን ለኢትዮጵያ የማለዱበት ወደ ዐርባ ዓመት የሚጠጋው ዝማሬ አለ፦

ኢትዮጵያን ኀብኛት ተመልከታት
በቃል ኪዳንህ አስባት

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅም ለ‹‹እናት ሐገር›› መፈወስ በዝማሬ ያቀረበው ጸሎት አለ፦

ባለ ብዙ ምሕረት ነህ ባለ ብዙ ይቅርታ
ፈውሳት ኢትዮጵያን አቤቱ ኢየሱስ የእኛ ጌታ።

### 2.4.1.4 የንስሓ/ የኑዛዜ ዝማሬ

የንስሓ ጸሎት በንግግር እንደምናቀርብ ሁሉ፣ የንስሓ ጸሎት በዝማሬ እናቀርባለን። በዝማሬውና በሕይወቱ በብሉይ ኪዳን እንደ ሞዴል የሚታየው ንጉሡና ዘማሪው ዳዊት በአንድ ወቅት ሁለቱን ከዐሠርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያዎቹን ሁለቱንና የመጨረሻውን 10ኛውን ተላለፈ። እስራኤል በጦርነት በነበረበት ወቅት እርሱ በሰፈር ቀርቶ በሠገነት ሲንሸራሸር የሰው ሚስት ተመለከተና ተመኘ፤ ሲመኝ 10ኛውን ትዕዛዝ ጣሰ፦ ‹‹የባልንጀራህን ሚስት አትመኝ።›› በዚሁ ቢያበቃ ጥሩ ነበር ግን ቀጠለ። ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ወለደች፣ ማለትም አመነዘረ። እናም 9ኛውን ትዕዛዝ ጣሰ፦ ‹‹አታመንዝር።›› በዚሁ ቢያበቃ ጥሩ ነበር ግን አላበቃም። የምንዝርና ኃጢአቱን ለመሸፈን ሲል ባሏን ኦሪዮንን አስገደለው። በዚህም 1ኛውን ትዕዛዝ ጣሰ፦ ‹‹አትግደል።›› (ዐሥርቱ ትዕዛዛት በዘፀአት 20 ላይ ይገኛሉ።)

ተስፋዬ ጋቢሶ ለዚህ ይሆን፦

ኃጢአት ሥሩን ሰዶ ሳይጠነክርብኝ
ሳይታወቀኝ አድኅ ሞትን ሳይወልድብኝ
ንስሓ እንድገባ በጊዜ ገሥጸኝ ብሎ የዘመረው።

ለማንኛውም ንጉሥ ዳዊት እነዚህን ሦስት ታላላቅ ትዕዛዛት ከጣሰ በኋላ ማንም አላወቀብኝም ብሎ ይሁን እንጃ ተደላድሎ በቤቱ ተቀምጦ ነበር፤ ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ህልዎት ቢለየውም። እግዚአብሔር ናታን የሚባል ነቢይ ላከበትና ገሠፀው። ዳዊት የኃጢአቱ ጥልቀት ታየው። የሚከተለውን አስደናቂ የንስሓ ዝማሬ ዘመረ፦

ይህ ዝማሬ መቼና ለምን እንደተዘመረ በርእሱ ላይ ተገልጧል፦በአዲሱ መደበኛ ትርጉም እንደሚከተለው ቀርቧል፦

መዝሙር 51

የኃጢአት ኑዛዜ

ለመዘምራን አለቃ ዳዊት ወደ ቤርሳቤህ ከገባ በኋላ፣ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ የዳዊት መዝሙር

1 እግዚአብሔር ሆይ እንደ ቸርነትህ መጠን፣
ምሕረት አድርግልኝ፣
እንደ ርኅራኄህም ብዛት
መተላለፌን ደምስስ።

2 እኔ መተላለፌን አውቃለሁና
ኃጢአቴም ዘወትር በፊቴ ነው።

ዳዊት እንደ ልቤ የተባለው ፍጹም ስለ ነበረ አልነበረም። ነገር ግን ምልስና ፈጥኖ ንስሓ የሚገባ ስለ ነበረ ነው። ዝማሬዎቹም ይህን ያመለክታሉ።

በሐገራችንም በርካታ የንስሓ ዝማሬዎች አሉ። በዚህ ዐይነቱ ዝማሬም ቢሆን የአንበሳ ውን ድርሻ የሚወስዱት የድሮ ዝማሬዎች ናቸው። ቀደም ባለው ጊዜ የሚዘመሩ ዝማሬዎች ብብዛኛው የኑዛዜና፣ የንስሓ፣ ምሕረቱንና ይቅርታውን የመለመን ይበዛባ ቸው ነበር። ይኼ ሚዛናዊ እስከ ተደረገ ድረስ ምንም ችግር የለውም ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊም ወይም አዲስ ኪዳናዊም ነው።

መጥምቁ ዮሐንስም ሆነ ጌታችን ኢየሱስ እየሰበኩ የመጡት ‹‹መንግሥተ ሰማይ ቀርባለችና ንስሓ ግቡ የሚል ነው። ጌታችን ኢየሱስ ደጋግሞ የሚያሳስበው የንሳሓን አስፈላጊነት ነው። ‹‹እናንተም ንስሓ ባትገቡ ትጠፉላችሁ›› ( ) ይል ነበር። የሚጠፉት ኃጢአት ስለ ሠሩ ሳይሆን ከኃጢአታቸው ንስሓ ስላልገቡ ነው። ኑዛዜና ንስሓ የሚያስፈልገን በብዙ መንገዶች እግዚአብሔርን በኃጢአታችን ስለምንበድለው ነው። ፍጹማን ብንሆንና ኃጢአትን ፈጽሞ የማንሠራ ብንሆን የንስሓ ጸሎትም ሆነ የንስሓ ዝማሬ አያስፈልገንም ነበር። ግን በብዙ መንገዶች ከጽድቅ መንገድ ጎድለን እንገኛለን። ለዚህ ነው ሐዋርያው ዮሐንስ ‹‹ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናስታለን፤ እውነትም በእኛ ውስጥ የለም፤ ኃጢአታችንን ብንናዘዝ፣ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለንና ከዐመፃም ሁሉ ሊያድነን የታመነና ጻድቅ ነው›› (1ኛ ዮሐ 1፡ 8)።

የኑዛዜና የንስሓ ዝማሬዎችን አብዝቶ በመዘመር የሚታወቀው ደረጀ ከበደ ነው። ደረጀ ያለምንም መንፈሳዊ የቋንቋ ቅብና ማሰማመር ያለፈበትን፣ የሚያልፍበትን፣ የተፈተነበትን የሚፈተንበትን፣ ድካሙን፣ ትግሉን፣ ጦርነቱን፣ ተስፋ መቁረጡን፣ ወዘተ ይዘምራል።

ቃሌና አረማመዴ አንድ አልሆነም ጌታ ሆይ
አታስተካክለኝም ወይ? ይላል ቀደም ባለው ዝማሬው።

ያለፈው በደሌን ተወው ጌታዬ አደራ አታስታውሰው
እባክህ ዕድል ስጠኝና ልጅህ አደርገኝ እንደገና።

 

ምን ይሻለኛል አዬ ምን ይሻለኛል?
ከዚህ ሚች ሥጋ ማን ይለኛል?

ጌታ ሆይ ጨርቅህን ይዤ እማፀናለሁ
ካንተ ወዴት ከቶ እሄዳለሁ
ደጃፍህ ብኖር ተጥዬ
ክብሬ ነው ለእኔ ተስፋዬ

ለብዙ ዘመናት ሽንጤን ገትሬያለሁ
ስሰበር ስደማ ያላቅሜ እያየሁ
ከእግዚአብሔር ጋር ውጊያ ምንም አልጠቀመኝ
እጆቼን አነሣሁ አዝኖ ቢማርከኝ።

ተስፋዬ ጋቢሶም አስገራሚ የንስሓ ዝማሬዎች አሉት፦

እግሮችም የሉኝም ፊትህ ምቆምበት
ዐይኖችም የሉኝም አንተን የማይበት
የጠራኸኝ አምላክ ውርደቴን ተመልከት
ከገባሁበት ማጥ አውጣኝ ባንተ ምሕረት።

እኔ ነኝ ተራራው ትልቁ እንቅፋት
የሕዝብህ ጉስቁልና የድካሙ ምክንያት
ኦ! ምንኛ ይመራል የትዕቢቴ ጽዋ
ጌታ ሆይ ዝቅ አርገኝ ሳይገለኝ ፍሬዋ።

ሽዋዬ ዳምጤም የቆዩ ዝማሬዎቹ ኃይለኛ የንስሓ ዝማሬዎች አሉባቸው፦

ከጣራዬ በታች ጓዳዬ መቼ ነው ማከብርህ ጌታዬ /2x
መቼ ነው መቼ ነው መቼ ነው
በኑሮዬ ክብረህ ሚታየው /2x

1. ለአፌ በጉባኤ እጅጉን ውዴ ነህ
   ከጣራዬ በታች ለቤቴ ባእድ ነህ
   ከሚወዱህ ጋራ ከንፈሬን መጣለሁ
   ለብቻዬ ቤቴ ለጣዖት ሰዋለሁ  2 x

## 2.4.2 ለአማኞች የሚዘመሩ ዝማሬዎች

ከጌታ ቀጥሎ ሁለተኞቹ የዝማሬያችን ተደራስያን አማኞች ናቸው። አንድ ጥሩ ስብከት ወይም ትምህርት የሚያደርገውን ነገር አንድ ጥሩ ዝማሬ በተሻለ ሁኔታ ይሠራል። በተሻለ ሁኔታ ያልኩበት ምክንያት ስብከት ጥሩም ቢሆን በጽሑፍ ወይም በካሴት ወይም በሌላ መንገድ ካልተያዘ በስተቀር ብብዛኛው የመረሳት ዕድሉ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ተመሥርቶ፣ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ወዝቶ፣ በጥሩ ቋንቋ ተከሽኖ፣ በጥሩ ሙዚቃ ታጅቦ የሚቀርብ ዝማሬ ግን በሰው ልቡና የመታወስ ዐቅሙ ከፍተኛ ነው።

በመሆኑም ለአማኞች ከሚዘመሩ ዝማሬዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡- የማጽናናት፣ የማበረታት፣ የምክር፣ የተግሣጽ፣ የትምህርት፣ወዘተ ናቸው።

### 2.4.2.1 የማጽናናት ዝማሬዎች

የማጽናናት ዝማሬዎች በተለያዩ የሕይወት ውጣ ውረዶች በማለፍ ልባቸው ለዛለ፣ በበሽታ፣ በሐዘን፣ ተስፋ በመቁረጥ፣ በእጦት፣ በብቸኝነት ወዘተ ውስጥ የሚያልፉ ትን አማኞች የሚያጽናኑ፣ ዝማሬዎች ናቸው።

በተስፋዬ ጋቢሶ መዝሙሮች ብንጀምር

የጉስቁልና ዘመንህ ያልፍና
ችግር ስቃይህ ይታሰብና
ጌታ ዳግመኛ ይጎበኝሃል
አዲስ ሰው አርጎ ይለውጥሃል 2x

1. ጌታን ሲጠብቅ ታምኖ የኖረ
   ብርሃንን ሳያይ ማነው የቀረ
   የነፍስህ ጥማት ናፍቆትህ ሁሉ
   ጸንተህ ብትቆይ መልስ ያገኛሉ።

2. ተረስቻለሁ ተጥያለሁኝ
   ለምንም ነገር የማልጠቅም ነኝ
   ለምን ትላለህ ጌታ ያስብሃል
   በራሱም ጊዜ ከፍ ያደርግሃል።

የሚከተለው ዝማሬ በአንደኛ መደብ የተዘመረም ቢሆን አሁንም እጅግ የሚያጽናና ዝማሬ ነው። ይህም የተስፋዬ ጋቢሶ ዝማሬ ነው፡-

እጅግ ተቸግሬ ስማጸን አይተኸኝ
እኔ ካንተ ጋር ነኝ አትፍራ እያልከኝ
በመጽናናትህ ሞልተህ ደስታን ታስታጥቀኛለህ
የልቤ አምላክ ሆይ ለዘላለም ዕድል ፈንታዬ ነህ።

ሌላው ከዚህ ምድብ የሚፈረጅ የተስፋዬ ዝማሬ ያይሃል የሚለው ዝማሬ ነው፡-

ያይሃል፣ ያይሃል፣ ያይሃል
ያይሃል ኢየሱስ ያይሃል
ያይሃል በእውነት ያይሃል
ያንተ ነገር ይገደዋል
ሊታደግህም ይመጣል።

1. በምድረ በዳ ያለኸው
   እንደ አጋር ያነባኸው
   የሚያይህንስ ብታየው

ፍጻሜህስ ተስፋ አለው።

ጌታ ‹‹አጽናኑ፣ ሕዝቤን አጽናኑ›› (ኢሳ 40፡1) ይላል። ይህ መልእክት በወቅቱ በመከራና በስደት ለነበረችው ለእስራኤል የተባለም ቢሆን ዛሬም ላለነው አማኞች መጽናናት እንደሚያስፈልገን እግዚአብሔር ያውቃል። በወደቀች ዓለምና በክፋት የተሞላ ገዢ ባላት ዓለም ውስጥ እንኖራለን። እናም መጽናናት ያስፈልገናል። እንዲያውም ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር አብ የሚከተለውን አስደናቂ ስም ሲያወጣለት እንመለከታለን፦ ‹‹የርኅራኄ አባት፣ የመጽናናትም ሁሉ አምላክ›› (2ኛ ቆሮ 1፡3)።

ወደ ቤተ ክርስቲያን ጉባኤ የሚመጡ ብዙዎች በርካታ የተለያዩ ችግሮች፣ ጥያቄዎችና እንቆቅልሾች ያላቸው ናቸው። ሲመጡ መጽናናትን ፈልገው ነው የሚመጡት። እናም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ መራን በቃሉ ላይ የተመሠረቱ አጽናኝ ዝማሬዎችን ብንዘምር ጥሩ ነው። ነገር ግን ‹‹እግዚአብሔር ለእኔ ያደላልኛል፣ ለእኔ እንዳደረገው ለማናቸውም አላደረገላችሁም፣ የእኔ ይበልጣል ወዘተ ብንል አንዳንዱ በልቡ ‹‹ምን ይጠበስ ታዲያ?›› ሊለን እንደሚችል መጠርጠሩ አይከፋም።

### 2.4.2.2 የሚመክሩ/ የሚገሥጹ ዝማሬዎች

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት፣ በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማል›› (2ኛ ጢሞ 3፡ 16)። እንዲሁም በ2ኛ ጢሞ 4፡2 ‹‹ቃሉን ስበክ፣ ዝለፍ፣ ገሥጽ፣ ምከር›› ይላል። አንድ ጥሩ ዝማሬ አንድ ጥሩ ስብከት ማድረግ የሚችለውን ነገር ማድረግ ይችላል። ውጤታማናቱ ግን ከስብከት በእጅጉ ይበልጣል። ይህም መዝሙር ኪነ ጥበባዊ በመሆኑ በግጥሙ በዜማውና በሙዚቃው ጉልበት በሰው ልብና አእምሮ መቆየት የሚችል በመሆኑ ነው። ስብከት ግን ካልተቀረጸ ወይም በማስታወሻ ካልተያዘ በስተቀር አብዛኛው መልእክት ይረሳል።

ከሚመክሩና ከሚገሥጹ ዝማሬዎች መካከል አሁንም የተስፋዬ ጋቢሶን ለአብነት እንውሰድ፦

በኩርነትህን ለምን ሸጥከው
የሱስን በምን ለወጥከው
ክብርና ገንዘብ ጠፊ ነው
የማይጠፋውን ምረጠው
ጌታ ይሻልሃል ለዘላለም ሕይወት ሚሆነው።

1. ለማያጠግብህ እሮጠህ
   ምናምንቴ ነገር ወደህ
   ረብ ረድኤት ለማይሆነው
   በኩርነተህን ሸጥከው።

2. ብዙዎች ወደቁ ተጠልፈው
   በገንዘብ ፍቅር ተነድፈው
   ብልጽግና ያታልላል
   ይሁዳ ጌታውን ሸጧል።

ከተስፋዬ የተገሣጽ ዝማሬዎች መካከል በተለይ ወደ አገልጋዮች የተነጣጠሩ ዝማሬዎ ችም አሉ፦ የአደባባይ ሰው ሆነህ፣ የጠፋውን ማን ይፈልጋል?

### 2.4.2.3 የሚያስተምሩ ዝማሬዎች

በሥርዓቱ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ጥሩ የወንጌል መልእክት አማኞችን እንደሚያ ንጽና እንደሚያስተምር በቃሉ ላይ ተመሥርቶ በጥሩ ሁኔታ የሚዘጋጅ ዝማሬም ይህኑን በሚገባ ያደርጋል።

የተስፋዬ ጋቢሶ ዝማሬዎች አብዛኛዎቹ አስተማሪዎች ናቸው። ጥቂቶቹን እንመልከት።

ማሰሮው ሲሰበር ድብቁ ብርሃን ይወጣል
ድብቁ ብርሃን ይወጣል
ስንዴው ሲበሰብስ ቡቃያው ብዙ ያፈራል።
ጌታዬ፣ አምላኬ የተሰበረ ልብ ያሻኛል።

ሌላ ዝማሬ ብንወስድ፡-

ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው
በቅዱስ ቃልህ በመንፈስህም የቀደሰካቸው
ጌታዬ ሆይ በመቅደስህ
ከፍ ባለው ዙፋንህ
ስግደት ይቅረብልህ

1. ሕያዋን ልጆች ክቡር ድንጋዮች
   በበጉ ደም የተዋጁ ሰዎች
   ቤተ መቅደስ ለመሆን ታነጹ
   ማደሪያ ሆኑለት ለንጉሡ።

2. በዓለም አእላፋት እርካታ ያጡ
   ዝናህን ሰምተው ከሩቅ የመጡ
   በኃጥዓን ድንኳን ከሚቀመጡ
   ባንተ ማደሪያ መጣል መረጡ።

3. ካህናትህም በመለከቶች
   መዘምራን በዜማ ዕቃዎች
   ባንድነት ቃና ወጣ ድምፃቸው
   ከፍ አደረጉህ በምስጋናቸው።

4. በዘላለማዊው ምሕረቱ
   ልዑል ጎበኘን በቸርነቱ
   ጌታ ለሕዝቡ ሰጠ ሞገሱን
   ያምላኬ ክብር ሞላ መቅደሱን።

### 2.4.2.4 ከቤተ ለከበለሉ የሚዘመሩ ዝማሬዎች

 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

ከቤቱ ለኮበለሉ/ backslide ላደረጉት መመለስ በጸሎት እንደምንማልድላቸው ሁሉ ይህንኑ በዝማሬ ማድረግ እንችላለን።

ደረጀ ከበደ ለኮበለሉት እንዲህ ይዘምራል፦

ማዶ ማዶ እያየሁ ጠብቃለሁ
የጠፋው ዘመዴን ናፍቄያለሁ
ቢሄድም ይመለሳል
ባምላክ ተስፋ መች ይቆረጣል።

ተስፋዬ ጋቢሶ ለኮበለሉት ከዘመሩት ቆየት ያሉ ዝማሬዎች መካከል የባዘነውን ፈላጊ አምላክ የሚለው ይገኝበታል።

1. የጠራውን መስሎ መኖር መጋደሉን ፈርቶ
   የገባለትን ቃልና ተስፋንም ዘንግቶ
   የሙት ልጅ የነበረ ሰው ከጥፋት የዳነው
   የተሠዋለትን የሱስ ያን አዳኙን ከዳው።
   
   የባዘነውን ፈላጊ አምላክ የምሕረት አምባ
   ለጠፉትም የምታነባ
   ከሕይወት ወደ ሞት ከእረፍት ወደ ጭንቀት
   የሄደውን መልስ ባክህ ጌታ ወደ መንጋህ በረት።

ሸዋዬ ዳምጤ ኮብላዩን በሸለቆ እንዳለ ይቆጥረዋል።

በሸለቆ ያለህ ወንድሜ ሆይ
እጠብቅሃለሁ አትመጣም ወይ
ተራራውን ውጣው በጌታህ
ይሉኝታና ፍርሃት አይግዙህ።

## 2.4.2.5 ያለ ክርስቶስ ለሆኑቱ የሚዘመሩ ዝማሬዎች

የክርስቶስ ብርሃን ላልበራላቸው ወደ ጌታ እንዲመጡ በጸሎት እንደምንማል ድላቸው፣ እንዲሁም በቃል ምስክርነታችን እንደምንሰጣቸው ሁሉ በዝማ ሬም ይህንን ማድረግ ይቻላል። በርካታ ዘማሪዎች የጥሪ/ የምስክርነት ዝማ ሬዎችን ዘምረዋል።

ደረጀ ከበደ በርካታ፣ ጉልበታም የጥሪ ዝማሬዎች አሉት፦

ሮጦ ሮጦ ሳይደርስ የልቡ
ለሞተ አዝናለሁ ሳይሞላ ሐሳቡ
አንተስ በሕይወት ሰምተሃል ቃሉን
ፍርድ ባንተ ነው ብትረግጥ ማዳኑን።

1. ወንድሜ ስማ ቁም ነገር ምክሬን ላንተ የሚበጅ
   ሳትሆን ባንቀልባ ዐቅም ሳያንስህ እንደ ሕፃን ልጅ
   ሞት አጥልቶብህ መቃብር ውጦህ ትንፋሽህ ሳይቆም
   ጌታን ተቀበል ዋስህ አድርገው ሳትጠፋ ካለም።

2. ዕድሜ ጤዛ ነው ረጋፊ አበባ ባለም ስትኖር
   የጭንቅ የሥቃይ ዘመነ ለቅሶ ዋይታና ሽብር
   የእፎይታ ናፍቆት የሰላም ፍቅር ከላ በልብህ
   ጌታን ተቀበል እርሱ ታማኝ ነው ሁሉን ሊሰጠህ።

3. ታዲያ ምን አለ የሚያስጨንቅህ ላንተ ያቃተህ
   ሱስ ነው መዋተት ባሪያ አድርጎ አንተን የገዛህ
   ዝሙት ነው ስካር ያስፈራህ ጓዴ ካንተ አይለዮ
   ጌታን አማክረው እርሱ ሽሮታል ሕይወቱን ከፍሎ።

ሌላ የደረጀ የጥሪ ዝማሬ እንዲህ ይላል፡-

የመዳንህ ቀን ዛሬ ነውና
ነገ ከቶ ያንተ አይደለምና
ወንድሜ ዛሬ ወደ ፈጣሪህ ና

1. እረፍትን እፎይታን ፍለጋ
   ሮጠሃል መሽቶ እስከሚነጋ
   እጅግም ባዶ ነው።
   ለባዘነው ልብህ እርካታ
   ዞር በል ያሳርፍህ ጌታ
   አትሁን ከርታታ።

ዳንኤል አምደ ሚካኤልም በመጀመሪያው አልበሙ ላይ እንዲህ ይጣራል፡-

እረ ተው ወንድሜ ችላ ችላ አትበል
ሕይወት ቀልድ አይደለም
ይብቃ ዝላዩ ጌታን ተቀበል
እረ ተይ እህቴ ችላ ችላ አትበይ
ሕይወት ቀልድ አይደለም
ይብቃ ዝላዩ ጌታን ተቀበይ።

**2.4.3** በተለያዩ ክርስቲያናዊ፣ማኅበራዊና መሰል ርእሰ ጉዳዮች ላይ የሚዘመሩ

**2.4.3.1** የሠርግ ዝማሬዎች

አማኞች በቅዱስ ጋብቻ በሚጣመሩበት ቀን የሚዘመሩ ዝማሬዎች የጋብቻን ክቡርነት የሚያስተምሩ ቢሆኑ የተመረጠ ነው። ብዙ በጌታ ያልሆኑ ሰዎች በሠርግ ስለሚታደሙ ይህን ከግንዛቤ ያስገባ ዝማሬ መዘመር ጥሩ ነው።

የሱስ ጥሪውን ወደደ
ቃና ዘገሊላ ወረደ
ሠርጉን ጣፋጭ አደረገው
በታምራቱ ቀደሰው።
(መካኒሳ መካነ የሱስ ህ መዘምራን)

የሠርግ ዝማሬ ያላቸው ብዙ ኳየሮች አሉ። ጌታ ያውቃልና ብሩክታይት በዚህ ርእስ ላይ ብቻ የሚያጠነጥን አልበም አላቸው።

### 2.4.3.2 የትዳር በረከት ዝማሬዎች

ስለ ክርስቲያናዊ ጋብቻ በረከት የሚናገሩ በትዳር ሕይወት ላይ ላሉ ምክር፣ ማሳሰቢያና ማንቂያ የሚሆኑ ዝማሬዎች ናቸው።

የዚህ ጽሑፍ አዘጋጅ አንድ ባል ያለበትን ኃላፊነት መወጣት እንዲችል ጌታ እንዲረዳው በሚተለው ዝማሬ እንዲህ ይጸልያል፦

እንደ ወደድካት አንተ እስከ ሞት ቤተ ክርስቲያንን
እንድወዳት እርዳኝ እስከ ሞት የትዳር አጋሬን

1. በጎ እንዳይደለ አይተህ ለብቻ መሆኔ
   ምትመቸኝ ረዳት ብትሰጠኝ ከጎኔ
   እንዳላመሰግንኩ እንዳልጨፈርኩ ያኔ
   በትንሽ ፈተና ዛሬ አልበል ወይኔ።

2. በደስታ፣ በሐዘን፣ በማግኘት፣ በማጣት
   ልንከባከብና ልጠነቀቅላት
   ባንተና በሕዝብህ ፊት ቃል እንደገባሁኝ
   በቃሌ እንድጸና ቆሜ እንድገኝ እርዳኝ።

3. ሰው አባት እናቱን ሁሉን ነገር ትቶ
   ከሚስቱ ይጣበቃል ያፈቅረታል ተግቶ
   ብለህ ያልከውን ቃል እንድፈጽመው
   አንተ ያጣመርከውን እንዳይለየው ሰው።

4. ነቀፊታና ነውር እንዳይገኝባት
   በደምህ አንጽተህ ቤትክን ቀደስካት
   ልከተል ፈለግህን ልሙት በየዕለት
   በቁጣ በጩኸት አይሠራም ቤት።

### 2.4.3.3 የልጆች በረከትና የማሳደጉ ኃላፊነትና ተግዳሮት

ስጦታዎቼ ከአምላኬ ያገኘኋችሁ
እደጉ ልጆቼ ኢየሱስ ያሳድጋችሁ
ከዘመኑ ዐመጽ በደሙ ጋርዶ ያውጣችሁ
ለእኔ እንደ ቆመ ለእናንተም ይቁምላችሁ።

1. አደራ ናችሁ ከእግዚአብሔር ወደ እኔ የተላካችሁ
   ስሙን በእናንተ እንዳኖር ፍቅሩንም እንዳሳያችሁ
   የፍቅሩ መገለጫዎች የአምላኬ ልዩ ስጦታ
   ለዘላለሙ ይባረክ እናንተን የሰጠኝ ጌታ።

2. ግሩም ነው ጌታ አሠራሩ እናንተን ብቻ መች ሰጠኝ
ፍቅርንም በውስጤ አኑሯል እንድወዳችሁ ሚያደርገኝ
ለእናንተ ያለኝን ፍቅር ሳይ ፍጹም ፍቅሩን አስባለሁ
ቸርነት ምሕረቱ ታውሶኝ የፍቅር ዕንባ አነባለሁ።

3. ፍቅራችሁ ትዝታዬ ነው እርቄ በሄድኩኝ ጊዜ
ሳላያችሁ ውዬ ካደርኩ ልቤ ይሰማዋል ትካዜ
ሳቃችሁ ብቻም አይደለ ይናፍቀኛል ለቅሷችሁ
ጸጥታው ይጮህብኛል ላፍታ ከፊቴ ሳጣችሁ።

4. እውነቱን ነግራችኋለሁ ፍርሃትም አለ በውስጤ
ዘመኑ እየከፋ ሲሄድ እየጨመረ ነው ምጤ
አደራ ሰጥቶኛልና በእርሱ ፍርሃት እንድታድጉ
ከዘሙኑ ዐመጽ ለማምለጥ ልጆቼ አምላኬን ፈልጉ።

5. ክፉ መካሪ በርክቷል ክፉ አስተማሪም ሰልጥኗል
ሥልጣኔውም ሰይጥኖ አምላክን ሊያስክድ ዶልቷል
አምላክ የለሽ ነው ትምህርቱ፣ ባሕሉ፣ ሳይንሱ እውቀቱ
ትውልዱን ታደገው ጌታ ፈጥነህ ታደገው በብርቱ።

6. ሁሌ ስለ እያንዳንዳችሁ ባምላኬ ፊት እቆማለሁ
ስማችሁን እየጠራሁ ስሙን በእናንተ አኖራለሁ
የአባታችሁን አምላክ ፍሩ በርቱ ልጆቼ ሰው ሁኑ
ከክፉ ሽሽታችሁ አምልጡ ክፉ ነውና ዘመኑ።

7. የአብርሃም የይስሓቅና የያዕቆብ አምላክ አድምጠኝ
የአባቶችን ዘር የባረክህ በል የእኔንም ዘር ባርክልኝ
አንተን በመፍራት ይደጉ ያንተን ጥበብ ሙላባቸው
እኔ ራሴን አላምነውም ይኸው ከእግርህ ሥር ጣልኳቸው።

### **2.4.3.4** የለቅሶ/ የሐዘን ጊዜ ዝማሬዎች

አካላዊ ሞት አዳም ለሰው ልጆች ሁሉ ያወረሰው ዕዳ ነው። ስለዚህ ሞት የሕይወት አንድ ገጽታ ነው። የምንወዳቸውን፣ የቅርባችን የሆኑትን በሞት እናጣቸዋለን። አማኝም፣ አላማኝም፣ ክፉም፣ ደግም፣ ሀብታምም፣ ድኻም፣ የተማረም፣ ያልተማረም፣ ሴትም ወንድም፣ ነጭም ጥቁርም ይኼኛውን ሞት ይሞታል፣ ጌታ ከዘገየ።

እንዲህ ከሆነ በቤተ ክርስቲያን አማኞች ወደ ጌታ በሚጠሩበት ጊዜ የሚዘመሩ ዐውዱን ያገናዘቡ ዝማሬዎች ቢኖሩ በጣም ጥሩ ነው። እንደ ሠርግ ጊዜ ሁሉ በለቅሶ ቦታም ሥነ ሥርዓቱም ለመታደም አማኙም አላማኙም ይሰበሰባል። ስለዚህ በዚህን ጊዜ የሚዘመሩ ዝማሬዎች ሞት ለአማኞች አስፈሪ

እንዳይደለ፣ ይልቁን ወደ ወደ ሞተላቸውና ዘላለማዊ መኖሪያቸው ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር የሚሰበሰቡት ነው።

ተስፋዬ ጋቢሶ በማንኛውም ጊዜ ሊዘመር የሚችልም ቢሆን በተለይ በለቅሶ ሥርዓትም ቢዘመር ተገቢነት ያለው ዝማሬ አለው። እንዲህ ይላል፡-

ነፍሴ ወዳምላኳ ሥጋም ወዳፈሩ ሳይመለስ
ቶሎ ቶሎ ብዬ ሥራዬን ልጨርስ
ነፍሴ ወዳምላኳ ሥጋም ወዳፈሩ ሳይመለስ
ሌት ተቀን ልትጋና ሥራዬን ልጨርስ።

1. ሲተጉ የሚያገኛቸው ሲመጣ ጌታቸው
በመክሊታቸው የተጉ ምስጋና አላቸው
አገልግሎቱን ያልናቀ በጥቂቱ ታምኖ
ብድራቱን ይቀበላል ሥራው ተተምኖ።

2. ጥቂት ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት
እንደ ሆነ መች አጣሁት ከቶ የእኔ ሕይወት
እንግዲያውስ ታከተኝ ሳልል ልሩጥ ለጌታዬ
የሰነፍ ሰው ሞት እንዳልሞት ልትጋ ባላማዬ።

3. መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ አበቃሁኝ
ሀይማኖቴን ጠብቄያለሁ ሩጫውን ጨረስኩኝ
እንደ ጳውሎስ ለማለት ተፈጸመ እንደ የሱስ
ምስጋናዬንም እንዳቀርብ ለሰራዊት ቅዱስ።

ደረጀ ከበደም ያለ ጌታ ወይም ጌታን ትተው ለሚሞቱ የሚሆኑ ዝማሬዎች አሉት። አንድ ሁለቱን እንመልከት፡-

1. ፕላን ያወጣና ሰው ለሺህ ዓመት
ሳያስበው ያልፋል ከመቅጽበት
ደካማ ማን አለ ሰውን መሳይ
የቅርቡን ሳያጣራ እሩቅ የሚያይ

ውብት ሲጠፋ ተመልከቼ ዝና
ላይጠቅም ተገንዝቤ
ተረዳሁኝ ሰው ለካ ከንቱ ነው።
ረጋፊ እንደ አበባ
ወዳፈር ሊገባ

2. በመጨሻው ቀን ሮጦ ሮጦ
ላይበጀው ካምላኩ እጅ አምልጦ
ይቀርባል ዙፋን ፊት መልስ ሊሰጥ
ላያመልጥ ቅጣት ሲሮጥ ሲሮጥ።

ታምራት ኃይሌም፡-

1. እንገናኝ ነገ እንገናኝ ደህና
ዛሬን ለማደሩ መች ዐወቀውና…ሰው ከንቱ

መንገዱን ሲያረዝም እቅዱን ሲያሰፋ
ዘንግቶት ይሆናል ታይቶ እንደሚጠፋ ሰው ከንቱ
ሰው ከንቱ ሰው ከንቱ
ሰው ከንቱ ሰው ከንቱ
ሰው ከንቱ ሰው ከንቱ
ጌታ ብቻ ከንቱ።

2. ጀግና ወጥቶ ሲቀር ጎበዙ ሲቀጠፍ
ነገን እያሰቡ ከዛሬ አለማለፍ ሰው ከንቱ
ብይ ጠጭ እያለ ነፍሱን ሲያዝናና
ሞት እንደ ደራሽ ወንዝ ድንገት ይመጣና።

3. ይህ ለእኔ ያም ለእኔ እዚህም እዚያም እኔ
ካለው ካገደመው ሲቅበዘበዝ ዐይኔ ሰው ከንቱ
የእኔ እገሌ ዘር ነኝ ሀብቴም እንዳፈር
ማንና ምን ይሆን አብሮኝ ሚቀበር ሰው ከንቱ

4. በውበት መመካት እውቀት አለኝ ማለት
ሕልም ሆኖ ሊቀር ካፈር የገቡ ዕለት ሰው ከንቱ
አስተዋይ ከዛሬ የነገን ይመርጣል
እግዚአብሔርን ማወቅ ከሁሉም ይበልጣል።

### 2.4.3.5 ክርስቲያናዊ ኅብረት

ክርስቲያናዊ ኅብረት ወይም ደግሞ የወንድሞችና የእህቶች በአንድነት መሆን የክርስትና ትርጉምና ኃይል ነው። ጌታችን የመጨረሻውን ሊቀ ክህነታዊ ጸሎት በምድር ላይ ባደረገባት በዚያች ምሽት አጠንክሮ ሲማልድ የነበረው ስለ ቅዱሳን/ አማኞች አንድነት/ ኅብረት ነበር። ምክንያቱም በክርስቶስ ከሆነ አንድነትና ኅብረት ውጪ ትርጉም ያለው ክርስትና የለምና። ዲያብሎስ ይህን ስለሚያውቅ ነው የማያቋርጥ ፍላጻ በቅዱሳን አንድነትና ኅብረት ላይ የሚያነጣጥረው።

ስለዚህ የከበረ መንፈሳዊ እሴት መዝሙሮቻችን ሊዳስሱ ይገባል። ተስፋዬ ጋቢሶ በዚህ ርእስ የዘመረውን አንድ ዝማሬ ለአብነት እንጥቀስ፦

ኅብረት አለን እኛስ በጌታ
ባምላካችን ቀረ መኖር ለየብቻ
ስሙ ይክበር የእኛ ጌታ።

1. ከምስራቅ፣ ከምዕራብ፣ ከደቡብ ከሰሜን
ከነገድ ከቋንቋ ከወገን ሰብስቦን
ልጁን በመሠዋት አምላክ አስታርቆን
ኅብረትን ሰጥቶናል ፍቅሩን አሳይቶን።

2. ማንም ያልሰጠንን አንድነት ሰጥቶናል
ከጥላቻ ሕመም ቁስሉ ፈውሶናል
ስለ መስቀሉ ቃል ሕይወታችን ፈስሶ
ለመሄድ ቆርጠናል ያ ቀናችን ደርሶ።

3. ያለም መልእክተኞች ሰላም ሰላም ሲሉ
ሲሸመጋገሉ፣ ለእርቅም ሲዋዋሉ
መሓላቸው ፈርሶ ይኼው ያለቅሳሉ
የእኛስ ኪዳን ጸንቷል በዚያው በመስቀሉ።

እንዲሁም በሌላ ተመሳሳይ መልእክት ባለው ዝማሬው እንዲህ ይላል፡-

ወንድሞች በኅብረት ሲቀመጡ ቀርበው
ለማነጽ ሚጠቅም የጸጋ ቃል ይዘው
አፋቸውን ሲከፍቱ በክርስቲያን ቋንቋ
ምንኛ ደስ ይላል ሲቀር አሉባልታ።

ጌታ ያውቃልና ብሩክታይትም

እጅ ለእጃችን ተያይዘን
ኢየሩሳሌም እንገባለን
በኢየሱስ ደም አንድ ሆነናል
አንለያይም ተዋደናል።

## 2.4.3.6 ቤተ ክርስቲያን

ቤተ የክርስቶስ ሙሽራ ነች። ክርስቶስ ዳግም መጥቶ ሊወስዳት ያለች ዓለም ውስጥ ዋና ንብረቱ ነች። ስለ ቤተ ክርስቲያን የተስፋ ቃሎች፣ ተጋድሎዎች፣ ድሎች ልንዘምር ይገባናል። የራእይ መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ሙሽራ የተዘመረ ዝማሬ ይዟል። እኛስ ምን ያህል የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን የተመለከቱ ዝማሬዎች አሉን?

ተስፋዬ ጋቢሶ ስለ ቤተ ክርስቲያን አሸናፊነት የሚከተለውን
ትንቢታዊ ዝማሬ ዘምሯል፡-

1. ዓላማ ይዞ የተሰለፈ የሚያስፈራው ያንተ ሠራዊት
ጠላቱን ሁሉ እያሸነፈ ባንተ መሪነት ቀንና ሌሊት
ባሕር ተሻግሮ በምድረ በዳ ጊኒጡን ረጋግጦ
ጥቂቱ ሕዝብህ ካንተ ጋር በዝቶ
ርስቱን ጨበጠ ከብዙ በልጦ።

ሕዝብህን አበዛህ ሕዝብህን አበዛህ
ያገሪቱንም ወሰን አሰፋህ

የማዳን እጅህን ለእኛ ዘረጋህ።

2. የሰናፍጪን ቅንጣት ቢዘራ
ጌታ በምድር እንድትበዛ
ያ ጉልበተኛ መጥቶ ረገጣት
የማትበቅል መስላው ፈዛዛ።
ግን አልተሳካም አምልጣ ወጣች
ሄደች አደገች
ጌታ ይመስገን ድንበሯ ሰፋ
ለደካከሙት መጠለያ ሆነች።

3. ኦ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ
እያሸነፈ ዘላለም ኗሪ
እንዳምላካችን ያለ ታዳጊ ከቶ የታለ ተወዳዳሪ
ጩኸትን ሰምቶ ምስኪን ድኾችን ዘይት የሚቀባ
ባደባባዩ በቤቱ ተክሎ የሚያለመልም እንደ ዘንባባ።

ታምራት ኃይሌም ተመሳሳይ መልዕክት ያለው ድንቅ ዝማሬ ዘምሯል፡-

1. የሉም ሲባል ይኖራሉ፣ ጠፉ ሲባል ይበዛሉ
ሲዋለዱ ብዙ መንታ ሩጫቸውን ማን ሊገታ
አይታክቱም ይሄዳሉ አይደክሙም ይበረታሉ
እንደ ንሥር ይበራሉ ዕጥፍ ድርብ ያፈራሉ።

እግዚአብሔር በልጁ ሞት የጠራው
ከነገድ ከቋንቋ ከሕዝብ የዋጀው
እርስቱ ነህ ሕዝቤ ገንዘቤ ያለው
ባለም ምድረ በዳ በድል የመራው
የታደለ ምስጉን ነው።

### 2.4.4 የአእማድ እውነቶች ዝማሬዎች

በክርስትና እምነት ውስጥ አእማድ/ ታላላቅ እውነቶች አሉ። አንዳንዶቹ የራሳቸው ጊዜ/ ካሌንደር አላቸው። ሌሎቹ የተለየ ቀን ባይኖራቸውም ራሳቸው ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

#### 2.4.4.1 የጌታ መወለድ

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ካደረጋቸው አስደናቂ ነገሮች አንዱ አንድያ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ ወደ ምድር በመላክ ለሰው ልጆች ኃጢአት መሥዋዕት እንዲሆን ማድረጉ ነው። በዚህ ነገር በጣም የሚደነቁት መላእክቱና ስለ አማኑኤል ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ናቸው (1ኛ ጴጥ 1፡10 -12)።

ስለ ጌታ መወለድ የተዘመሩ በርካታ ዝማሬዎች አሉ። አንድ ሁለቱን ለአብነት እንመልከት።

ምናልባት ከ35 ዓመታት ዕድሜ በላይ ያለው የመሠረተ ክርስቶስ ሀ መዘምራን የሚዘምሩት በጣም የሚታወቅ

ዝማሬ ነው፡-

የምሥራቹ ቃል በምድር ተሰማ
በከብቶች በረት ውስጥ ቤቴልሔም ከተማ
ምንም ጊዜው ቢረዝም ቢታይም ርቆ
የሱስ ተወለደ ዘመኑን ጠብቆ።

ሌላው የቆየ ዝማሬ

መላእክት ዘመሩለት ሰማይም ደመቀ
የሱስ መወለዱ ለድኾች ታወቀ
መንፈስ የጸለለው የከበረው ሕፃን
መድኅን ተወለደ ከኃጢአት ሊያነጻን።
እልል እንበል እልል እንበል
እንዘምር በደስታ መቸገራችንን አይቶ
ወረደልን ጌታ።

## 2.4.4.2 ሕማማቱ፣ ሞቱ፣ ትንሣኤው፣ ዕርገቱ

የጌታ ሥቃይ፣ ሞትና ትንሣኤ እንደ ልደቱ ሁሉ ከድነታችን ጋር በጥብቅ የተቆራኙ በጣም ትላልቅ እውነቶች ናቸው። ቀደም ብለን ስለ ውዳሴያችን ትኩረቶች ስንነጋገር እንደ ጠቀስነው እግዚአብሔርን ከምናመሰግንባቸው ሦስት ዐበይት ሥራዎቹ (ፈጣሪነቱ፣ አዳኝነቱ፣ እና መግቦቱ) አንዱ አዳኝነቱ ነው።

ቀደም ብለን በከፊል ስለ ጠቀስን በዚህ ቦታ ሁሉንም በዝርዝር አንመለከትም። አንድ የደረጀን ዝማሬ ብቻ እንጥቀስ። በዚህ ዝማሬ ደረጀ ሞቱን፣ ትንሣኤውን፣ ዳግመኛ ምፃቱን እዘምራለሁ ይላል። ነገር ግን በዝማሬው ከዚያ ያለፈ ነገር ነው የሚያደርገው። ስለ መወለዱ፣ ስለ ሕማማቱ፣ ስለ ሞቱ፣ ስለ ትንሣኤውና ስለ ዕርገቱ ይተርካል።

ዝም አልልም አወራለሁ ታሪኩን
ዝም አልልም እናገራለሁ ገድሉን
ሞቱን ትንሣኤውን ዳግመኛ ምጽአቱን።

1. ሰው ጎስቋላ ሆኖ ኃጢአቱ ውጦት
የእግዚአብሔር ልጅ ከላይ በሐዘን ተመልክቶት
ሊያድነው ወደደ ክብሩን ትቶ መጥቶ
ሥጋ ለብሶ እንደ ሰው ከሰው ማሕፀን ወጥቶ።

2. ጊዜው ደረሰና ግርግም ተወልዶ
ዓለምን ሊዋጃት ሆነ ምስኪን ባዶ
ሙታንን አስነሣ ለዲዳው አፍ ሰጠው
ዕውሩን አበራ ለምጻሙን ዳሰሰው።

3. ሰው ግን አልፈቀደም አዳኙን ሊቀበል

 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

ክፉቱ ገፋፋው ሊሰጠው ለመስቀል
በርባንንም ተፈታ የሱስ በእግሩ ገባ
ስለ ሰው ኃጢአት የደም ዕንባ አነባ።

4. መቃብሩ ተናጋ ሳይቆይ በሰለስቱ
ከሙታን ተለየ እንዳምላክነቱ
ሄደ ወዳባቱ ዐረገ ወደላይ
እመጣለሁ ብሎ ልፈርድ ባለም ላይ።

## ማጠቃለያ

የዝማሬ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ ቁልፍ ሚና አለው። ቀደም ብለን እንዳየነው በዝማሬ ጌታን እናወድሳለን፣ እናመልካለን። ጌታን ማምለክ ከሁሉ የላቀው የቤተ ክርስቲያን ጥሪ ነው።

በመቀጠል የሚመጣው አካሉን የማነጽ አገልግሎት ነው። በቃሉ ላይ ተመሥርተው በሥርዓቱ የተዘጋጁ ዝማሬዎች ያስተምራሉ፣ ያጽናናሉ፣ ይመክራሉ፣ ይገሥጻሉ። እንዲሁም ዝማሬዎች ትልቅ የወንጌል ማሠራጫ መሣሪያዎች ናቸው። የሐገራችንን ዐውድ እንኳ ብንመለከት በጥናት ባይረጋገጥም ወደ ጌታ ከሚመጡት ሰዎች ምናልባት ከ70 ከመቶ በላይ የሚሆኑቱ በዝማሬ ተማርከው የመጡ ናቸው። ስለዚህ ቤተ ክርስቲያን ይህን ትልቅ አገልግሎት በሚገባ ልትጠቀምበት ይገባል። መዘምራንም ዝማሬ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ የሚጫወተውን ትልቅ ድርሻ በመረዳት በቃሉ ላይ የተመሠረቱ፣ ክርስቶስን ያማከሉ፣ ወጥ መልእክት ያላቸውን ዝማሬዎች ለመጻፍ መትጋት ይኖርባቸዋል።

# III. የጉባኤ አምልኮ የመምራት ጥበብ

## 3.1 መግቢያ

የጉባኤ አምልኮ መሪ/ መሪዎች በተሳሳተው ስያሜያቸው ‹‹አስመላኪ›› ይባላሉ። ስሙ ተገቢ ያልሆነው ማንም ማንንም ሊያስመልክ ስለማይችል ነው። ቅዱሱን አምላክ ለማምለክ የሚያስችለን መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። ሰዎች እንድንዘምር፣ እንድናጨበ ጭብ፣ እንድናሸበሽብ ሊያደርጉን ይችላሉ። መዘመራችን፣ ማጨብጨባችን፣ ማሸብሸባ ችን ግን በእርግጥ ለማምለካችን ዋስትና ሊሆን አይችልም። እውነተኛ አምልኮ የብዙ ነገሮች ድምር ውጤት ነው፤ በጭብጨባ፣ በሽብሸባና ሞቅ ባለ ሙዚቃ የታጀበ ሞቅ ያለ ዝማሬ መዘመር ብቻውን አምልኮን ሊፈጥር አይችልም።

የጉባኤ አምልኮ መሪ የሚባለው ቃሉና ተግባሩ ወደ ሐገራችን ከመጣ ምናልባት ሁለት ዐሥርታት ቢሆኑ ነው። ቀደም ባሉት ዓመታት የፕሮግራም መሪ ነበር የሚባለው። ኃላፊነቱ ከአሁኖቹ አምልኮ መሪዎች የተለየና የተወሰነ ነበር። የፕሮግራም መሪው ሃላፊነት ባብዛኛው የጉባኤ አምልኮውን በጸሎት መክፈት ወይም የሚጸልይ ሰው መጋበዝ፣ ከዚያም በዕለቱ ፕሮግራም ቅደም ተከተል መሠረት ወደ መድረክ ወጥተው የሚያገለግሉትን ሰዎች መጋበዝ ነበር። አምልኮ መምራት እንኳን ለማለት ባይቻል ዝማሬ ይመራ ነበር እንኳ ብንል የሚያደርገው ነገር ጉባኤው ዝማሬዎችን ወይም አዝማቾችን እንዲመርጥ አድርጎ እጁን እያወናጨፈ መምራት ነበር። መዘምራኑን ወደ መድረክ ወጥተው እንዲዘምሩ ይጋብዛል። እነርሱ አገልግሎታቸውን ሲፈጽሙ ሰባኪውን ይጋብዛል። ይኸው ነበር የፕሮግራም መሪው አገልግሎት ከሞላ ጎደል።

የአሁኑ አምልኮ መምራት ግን የተለየ ነው። አንድ ዋና የአምልኮ መሪ አለ፤ በእርሱ አመራር ሥር አምስት ወይም ሰባት ወይም የተወሰነ ቁጥር ያላቸወ አብረውት ቆመው ጉባኤውን በዝማሬ የሚመሩ መዘምራን አሉት። ጉባኤውን መዝሙር ማስመረጥ በአሁኑ ጊዜ የማይታሰብ ነው፤ ፈጽሞም አይታወቅም። የአምልኮ መሪ ቡድኑ በሳምንት ውስጥ ተገናኝቶ በአንድነት ጸልዮና ለጉባኤ አምልኮ የሚሆኑ ዝማሬዎችን ይዞ መጥቶ ጉባኤውን በአምልኮ ዝማሬ ይመራል። ከመደበኛው የመዘምራን አገልግሎት የሚለየው የአምልኮ መሪ ቡድኑ ኃላፊነት ጉባኤውን ወክሎ መዘመር ሳይሆን ጉባኤው በውስጡ ያለውን ምስጋናና ውዳሴ ለጌታ በዝማሬ እንዲያፈስ መርዳት ነው።

## 3.2 የአምልኮ መሪ መመዘኛዎች

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች ተመድበው ወይም የተወሰነ መስፈርት በማሟላታቸው ተመርጠው ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ፣ በብዙ ቦታዎች፣ የአምልኮ መሪዎች የሚመረጡት በዋናነት መዘመር ወይም ማስዘመር ስለሚችሉ፣ ድምፃቸው ጥሩ ስለሆነ፣ ሙዚቃ ስለሚችሉ ብቻ ይሆናል።  እነዚህ በራሳቸው ለአንድ አምልኮ መሪ አስፈላጊ ቢሆኑም የአምልኮ መሪ ሊያሟላቸው ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች የመጀመሪያም የመጨረሻም ግን አይደሉም። ጌታን የማያ ውቅ ሰው እንኳን እነዚህ ነገሮች ሊኖሩት ይችላሉና።

ብዙ ጊዜ በቃል ባይገለጥም እንኳን በውስጠ ታዋቂነት የጉባኤ አምልኮ ጊዜው በራ አስፈላጊ እንደሆነ ሳይሆን ወደ ቃሉ አገልግሎት መሸጋገሪያ ወይም ፕሮግራም ሟሟያ እንደሆነ ነው የሚታሰበው። እንደ እውነቱ ከሆነ ለጌታ ፍቅራችንን፣ ውዳሴያችንን፣ አምልኳችንን በዝማሬ፣ በጸሎትና በሌሎችም መንገዶች ከምንገልጽበት የሚልቅ ጉዳይም ሆነ አገልግሎት በጉባኤ አምልኳችን የለም። ስብከቱ እኛ የምንማርበት፣ የምንታነጽበት ነው። የጉባኤ አምልኮ ጊዜው ግን እግዚአብሔርን ስለ ማንነቱና ስለ ሠራቸው ሥራዎቹ የምስጋናችንን መሥዋዕት የከንፈራችንን ፍሬ በዝማሬ የምናቀርብበት ነው። ጊዜውም፣ አገልግሎቱም ተገቢ ክብር ሊሰጠው ይገባል፤ ለከበረው አምላክ የሚቀርብ መሥዋዕት ነውና። የጉባኤ አምልኮ ጊዜው ችግር ካለበት የቃል ጊዜውም ሆነ ሌሎቹ አገልግሎቶች ሁሉ ውጤታማ አይሆኑም። ስለዚህ ለዚህ የከበረ አገልግሎት የምናሰልፋቸው አገልጋ ዮች በጥንቃቄ ተመርጠው ሊመደቡ ይገባል። ዳዊት መዘምራኑን ያሰለፈው መርጦ መድቦ (ኦርዴይን) አድርጎ ነው (1ኛ ዜና 25)።

1ኛ. የአምልኮ መሪ በዋናነት አምላኪ መሆን አለበት። ይኼ ከሁሉ የላቀው መስፈርት ነው። ራሱ የማያመልክ ሰው ሌላውን በአምልኮ ሊመራ አይችልም። እኛ ያላየውን ልናሳይ፣ ወዳልደረስንበት ልናደርስ፣ ወደማናውቀው ስፍራ ልንመራ አንችልም።

2ኛ. የአምልኮ መሪው የተፈተነ መንፈሳዊ ሕይወት ያለው ሊሆን ይገባል። አዲስ ክርስቲያን አይሁን እንደሚለው ጳውሎስ ማለት ነው።

3ኛ. ተቀባይነት ያለው የሙዚቃ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል። የዝማሬ አገልግሎት በሙዚቃ ስለሚታጀብ ቢያንስ መሠረታዊ የሆኑ የሙዚቃ አላባውያንን ማወቅ ይኖርበታል፦ እንደ ምት፣ ፒች፣ ባር መጠበቅ ወዘተ።

4ኛ. መልካም ስምና መልካም ምስክርነት ያለው ሊሆን ይገባል። በዕለት ተዕለት ሕይወቱ፣ በትዳር ሕይወቱ (ያገባ ከሆነ) ነቀፋ የሌለበት ካልሆነ (የጌታን እንኳን ብንተወው) በጉባኤው ዘንድ አገልግሎቱ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም። ይህ ማለት አምልኮ መሪዎች ፍጹማን መሆን አለባቸው ማለት አይደለም። ነገር ግን በድፍረት በዐመጻ ሕይወት የሚመላለሱ፣ ንስሓና የንስሓ ፍሬ የማይታይባቸው ሊሆኑ አይገባም ማለት ነው።

5ኛ.  አምልኮ መሪው ቤተ ክርስቲያኑንና መሪዎቿን የሚወድና የሚያከብር መሆን አለበት። ለቤተ ክርስቲያኒቱ አስተምህሮና ለመጋቢው ድብቅ ጥላቻ ካለው አምልኮ መምራትን የመሰለ አገልግሎት ውስጥ ሊሣተፍ አይገባውም። ይልቁን ንስሓ መግባት ይገባዋል።

6ኛ. አምልኮ መሪው የተነቃቃ፣ ተግባቢና ፏፏቴ የሚሉት ዐይነት መሆን አለበት። ኮስታራና ፊቱ የማይፈታ ከሆነ ከፍትፍቱ ፊቱ የሚል ብሒል ያለውን ምዕመን በአምልኮ ሊመራ ይቸገራል፤ ጥሩ ምላሽ ማግኘት ስለሚሳነው።

## 3.3 የአምልኮ መሪው ዝግጅት

ዋናውና ከሁሉ የላቀው የአምልኮ መሪ ዝግጅት መደበኛ የጸሎት ጊዜ በመለየትና  የጸሎት ሕይወትን በማዳበር ዘወትር ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ንቁ ውስጣዊ ጆሮ ይዞ  መምጣት ነው። ይህም አምልኮ መሪው ራሱ በቅድሚያ ጌታን ለማምለክ የግል የጥሞና  ጊዜውን በትጋት የሚጠብቅ ሊሆን ይገባል ማለት ነው። ብቻችንን ቤታችን ሆነን    እርሱን ማምለክ ከተለማመድን በጉባኤ ፊት ስንወጣ ብዙ ግብ ግብ

 እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል (ዮሐ 4፡24)።

አይገጥመንም። በጥሞና ጊዜያችን በስውር የዘራነውን በጉባኤ አምልኮ ወቅት በይፋ እናጭዳለን ማለት ነው።

ሁለተኛው ዝግጅት የተወሰነ ቀንና ሰዓት ወስኖ ለሳምንታዊው የጉባኤ አምልኮ የመምራት አገልግሎት መዘጋጀት ነው። ቅዳሜ ምሽት ወይም እሑድ ማለዳ ጊዜ ወስነን በግላችን ማወደስና ማምለክ ያስፈልጋል። ይህም ወደ መቅደሱ ስንገባ ወዲያው እንድንቀጣጠል ያስችለናል። ያ ጊዜ የግላችንን ጥርመሳ እያካሄድን የጉባኤውን ጊዜ የምንጨርስበት መሆን የለበትም። እና ተለኩሰንና ፈጥነን ገብተን ሕዝቡን ወደ ጽዮን ተራራ (ወደ ቅድስተ ቅዱሳን) ይዘን የምንገሠግስበት ጊዜ ነው።

ሦስተኛው የድምፅ ዝግጅት (ቮካል ኤክሰርሳይስ) ማድረግ ነው።

አራተኛው ዝግጅት የሚቻል ሲሆን በቅድሚያ ከመጋቢው ጋር ወይም የዕለቱን ፕሮግራም ከሚያስተባብረው ሰው ጋር ተገናኝቶ ስለ ዕለቱ አገልግሎት መነጋገር ጥሩ ነው።

አራተኛው ቀደም ብለን ወደ አምልኮ ቦታው መድረስ ጊዜው ደርሶብን ከመደነባበር ያድነናል።

## 3.4 አጠቃላይ መመሪያዎች

### 3.1 ዝግጁ ሁን፡-

ቀድመህ በመገኘት እምነት የሚጣልብህና የመጋቢውን ልብ አሳርፍ፤ የጉባኤውን ይሁንታ አግኝ። ቁና ቁና እየተነፈስክና እየተደነባበርክ ወደ መድረክ ከወጣህ የአምልኮው አገልግሎት ትልቅ ችግር ገጥሞታል፡- ያም ችግር አንተው ራስህ ነህ።

### 3.2 ራስህን ሁን፡-

ማንንም ለመኮረጅ አትሞክር። ከጥሩ አምልኮ መሪዎች መማር የምንችላቸው ነገሮች አሉ። እነርሱን ለመምሰል ግን ራሳችንን መጣል የእኛ የግላችን የሆኑትን ባሕርያታችንን መተው የለብንም። ይኼ አርቲፊሻል ያደርገናል። ተቀባይነታችንንም ያሳጣናል።

### 3.3 አንድ መሪ ጭብጥ ወይም ሐሳብ ከያዝክ ወዲያው ወደ ሌላው ለመሸጋገር አትጣደፍ።

መንፈስ ቅዱስ የጀመረውን እንዲጨርስ ዕድል ስጠው። ዞሮ ዞሮ ዋናው የአምልኮ መሪ እርሱ ነውና ከእርሱ ሰምቶ ማድረግ ብቻ ነው ውጤታማ የሚያደርገን። አለዚያ ፕሮግራም መሪ ብቻ ሆነን እንቀራለን። በብዙ ዝማሬ መንበሽበሽ የግድ አይደለም። ለየዕለቱ መንፈስ ቅዱስን በሚገባ ካደመጥነው የራሱ ልዩ ትኩረት ይኖረዋል። ያን አውቀን ስንከተል ጉባኤውም እኛም በጽዮን ከፍታዎች ላይ ቆይታ የማድረግ ዕድላችን ትልቅ ይሆናል።

### 3.4 በጊዜውም ያለጊዜውም ዝግጁ ሁን። ባወጣኻቸው የመዝሙር ዝርዝሮች ላይ የሙጢኝ አትበል።

ለሁሉም ጊዜ የሚሆኑ አዝማቾች ወይም ዝማሬዎች ይኑሩህ። በድንገት ባልጠበከውና ልተዘጋጀህበት
ርእሰ ጉዳይ አምልኮውን በዝማሬ እንድትመራ ልትጋበዝ ትችላለህ። ፈጠን ያለ ውሳኔ በማድረግ

ለወቅቱና ለጊዜው ተስማሚ የሆነውን ነገር ማድረግ ይኖርብሃል።

**III.5** መሪ እንጂ ተቆጣጣሪ አትሁን።

የአምልኮ መሪ ማለት የሙዚቃ ኮንዳክተር ማለት አይደለም። ሕዝቡ እኛ የምንፈል ገውን ብቻ እንዲያደርግ ለማድረግ ማኒፑሌት ማድረግ (መሸንገል) አይገባም። ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲያወድስ ማበረታት መቆስቆስ አንድ ነገር ነው። መሸንገልም ሆነ ዛቻ ወይም ከዚያ ያለፈው ነገር ተገቢ አይደለም። የመጨረሻ ውጤቱም አሉታዊ ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ እንኳን ይመራናል እንጂ አይቆጣጠረንም። እኛ ሕዝቡን የምንቆጣጠር ታዲያ እኛ ማን ነን?

**III.6** የሰዎችን ትኩረት እንድትስብ የሚያደርጉህን ነገሮች በተቻለ መጠን ቀንስ።

‹‹ጌታው የሱስን ልናይ እንወዳለን›› ()። ሙሽራይቱ ሙሽራዋን ለማየት ነው የምትናፍቀው። ዐይኖቿን ከሙሽራው ላይ አንሥታ እነርሱ ላይ እንድታደርግ ለሚሹ ሚዜዎች ሙሽሪት ትዕግሥትም ጊዜም የላትም። አምልኮ መሪዎች ሆይ ውጤታማነታችሁ የሚለካው አቤት እንዴት ያለ ዘማሪ ነው፣ እንዴት ያለ አምልኮ መሪ ነው! እያሉ ምዕመናን ከጉባኤው ሲወጡ ሳይሆን እንዴት ያለ ታላቅና ቅዱስ ጌታ ነው! እያሉ ከጉባኤው ከወጡ ነው። ስለዚህ ራስህን ለማሳየት፣ ለመደነቅ የምታደርገውን መሯሯጥ አቁመህ የሙሽራይቱ ዐይኖች ወደ ሙሽራዋ መሆኑን አረጋግጥ።

ትኩረት ወደ ራስህ ላለመሳብ ልታደርጋቸው ከምትችላቸው ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦

ሀ. በድምፅ ማጉያው ላይ ከልክ በላይ አትጩህ።

ለ. መድረኩን የሩጫ ትራክ አታድርገው። መድረክ ላይ በፍጥነት የምትሯሯጥ ከሆነ ሰዉ ዐይኑን በአንተ ላይ እንዲተክል ታስገድደዋለህ። አላስፈላጊ ሩጫ መድረክ ላይ ባይበዛ ጥሩ ነው። ‹‹ወደ እግዚአብሔር ቤት በገባህ ጊዜ እግርህን ጠብቅ፤ ለመስማት መቅረብ ከሰነፎች መሥዋዕት ይበልጣልና›› (መክ 5፡1)።

ሐ. አልፎ አልፎም ቢሆን እንዲህ ሁኑ አንዲያ አድርጉ የሚል ትዕዛዝህን አቁመህ ራስህ በአምልኮ ውስጥ ጥለቅ። ጌታን ስትወደው፣ ትኩረትህን እርሱ ስቦት በናፍቆት፣በመንፈስ ወደ እርሱ ስትገሠግስ ይመለከቱህ። ይህ ከሆነ ምዕመናኑን የምትማርካቸው አንተ አትሆንም። አንተን ይተዉህና አንተን ወደ ማረከው በመንፈስ ይገሠግሳሉ። አምልኮ መሪ ጭንቀቱ ሁሉ ለጎናዊው አገልግሎት ከሆነ (horizontally minded ከሆነ) ማለትም ትልቁ ትኩረቱ ሕዝቡ መዘመሩ፣ ማሸብሸቡ፣ ሙዚቃው መድመቁ ብቻ ከሆነ ራሱ አምልኮ መሪ መሆኑ ቀርቶ አምልኮ አምላኪ ሆኗል ማለት ነው። ይህ እንዳይሆን የአምልኮ መሪዎች ዋና ትኩረት ዐምዳዊ (vertical) ሊሆን ይገባል። የአምልኮ ትኩረት ጌታና ጌታ ብቻ ሊሆን ይገባል። እርሱ ላይ ስናተኩር ብቻ ነው እኛ እውነተኛ በረከት የምናገኘው።

**III.7** የሚከተሉትን አታድርግ

ሀ. ሕዝቡ ካለበት ቦታ ጀምር።

ማለትም አንተ በአምልኮ ቆይተህ ተነቃቅተህ ከሆኑ ሁሉም ወዲያውኑ በዚያ ቦታ ላይሆን ይችላል። ብዙ ሰዎች በሳምንቱ ኑሮና ሥራ በሥጋ፣ በነፍስ፣ በመንፈስ፣ በስሜት፣ በአእምሮ ዝለው ነው የሚመጡት። ስለዚህ አምልኮ መሪው እንደ መልካም እረኛ በጎቹን በመንፈስ ቅዱስ በመመራት በአምልኮ ወደ ለምለም መስክና ወደ እረፍት ሊመራቸው ይገባል።

ለ. በዝማሬ ከመራህ በኋላ ሕዝቡ ወደ አምልኮ እንዲገባ ዕድል ስጠው። መዝሙር መምራትና አምልኮ መምራት ይለያያል። መዝሙር ለመምራት መዝሙሩን ማወቅ ብቻ በቂ ሊሆን ይችላል። አምልኮ መምራት ግን የምና መልከውን አምላክና ዋናውን የአምልኮ መሪ መንፈስ ቅዱስን በሚገባ ማወቅ ይጠይቃል። መንፈስ ቅዱስ ለወቅቱ ያለውን ሐሳብ ስናውቅ በቀላሉ ጥልቅ ወደሆነ አምልኮ መጥለቅ ሕዝቡንም መምራት እንችላለን።

ሐ. ሕዝቡ የሚያውቃቸውን ዝማሬዎች አስዘምር። አንተ አምልኮ መሪ እንጂ ሶሎይስት ወይም ኳየር አይለህም። ሕዝቡን ወክለህ እንድትዘምርላ ቸው ሳይሆን ውስጣቸው ያለውን ውዳሴ እንዲያፈሱ ነው ልትረዳቸው የሚገባህ። እንደ አምልኮ መሪ ውጤታማ የምትሆነው አንተ ጥሩ አድርገህ ስለ ዘመርክ ሳይሆን ሕዝቡ ጥሩ አድርጎ እንዲዘመር ከረዳኸው ብቻ ነው።

መ. ክርስቶስን ያማከሉ ዝማሬዎችን ምረጥ። ለጉባኤ የሚሆን ዝማሬ ስትመርጥ መመዘኛህ በጣም ታዋቂ ወይም ዝነኛ ዝማሬ መሆኑ፣ ወይም ደግሞ ለእንቅስቃሴ የሚመች መሆኑ ሊሆን አይገባም። ይልቁን የመዝሙርዝቡ ዋና መልእክት ምንድነው? በመዝሙሩ ውስጥ ጎልቶ የሚታየው ‹‹እኔ›› ወይም ‹‹እኛ›› ነው ወይስ ‹‹እርሱ›› ወይም ‹‹አንተ/ ጌታ›› ነው? አንዳንድ ኑፋቄ የሚያስተምሩ ዝማሬዎች እንዳሉ መረዳት ይኖርብናል። ስለዚህ ለጉባኤ አምልኮ የምትመርጣቸውን ዝማሬዎች ወይም አዝማቾች በብዙ አቅጣጫ መገምገም አስፈላጊ ነው።

ሠ. ሙሉ ዝማሬዎችንም ለማስዘመር ትጋ። አዝማቾችን መቀጣጠል ለአምልኮ ፍሰት ጥሩ ቢሆንም ሙሉ ዝማሬዎችን መዘመር የመዝሙሩን ሙሉ መልእክት ለማግኘት ያስችላል። ዘጠኝ ዳቦ ከመላስ አንዱን መቅመስ/ መግመጥ እንደሚባለው ማለት ነው።

### III.8 የሚከተሉትን አታድርግ

ሀ. በሚገባ ያልዘመረ ከመሰለህ ሕዝቡን ማበረታት እንጂ ማመንጫጩቅ ፈጽሞ የለብህም። ሕዝቡ እግዚአብሔርን ሊያመልክ የሚያስችለውን ምቹ ሁኔታ ከፈጠርክለት በኋላ ያን ዕድል ተጠቅሞ ማምለክም ሆነ አለማምለክ የእርሱ ፋንታ ነው። አምልኮ በውዴታ እንጂ በግዴታ አይደለም። ጌታ የማያስገደድ ከሆነ እኛ ለማስገደድ የምንሞክረው ለምንድነው?

ለ. ሕዝቡን ተገቢ ያልሆነ ትእዛዝ አትዘዘው። አጠገብህ ያለውን ሰው እጁን ጨመቅ አድርገህ ይዘህ፣ ዐይን ዐይኑን እያየህ….በለው። አትፍዘዝ በለው… ባጭሩ እንዲህ ዐይነቱ የመድረክ ባሕርይ ተገቢም አስፈላጊም አይደለም።

ሐ. እጆቻችሁን ወደ ጌታ አንሡ! ካልክ በኋላ እንዳታወርዱት አትበል። ሁላችሁም በእግሮቻችሁ ተነሥታችሁ ቁሙ ካልክ በኋላ እንዳትቀመጡ አትበል።

መ. የሙዚቃ መሣሪያዎቹ ከልክ በላይ እንዲጮሁ አታድርግ።

ሠ. የአምልኮ ፍሰትን አታቋርጥ። ማለትም መዝሙሩን አለጊዜው አታቋርጥ ወይም በፍጥነት አትቀያይር።

ረ. አትስበክ፣ ብዙ ወሬ አታብዛ። መናገር ካለብህ ጸልየህ፣ አስበህበት፣ በጣም አስፈላጊ ከሆነ ብቻ በአጭሩ ተናግረህ ወደ ዋናው ተግባርህ ተመለስ።

ሰ. ግዳይ እንደ ጣለ አንበሳ መድረኩ ላይ አትንጎማለል። ወይም እንደ አጭር ርቀት ሯጭ በመድረኩ ላይ በፍጥነት አትሩጥ።

ሸ. አንተም ማምለክ እንዳለብህ አትዘንጋ። ሕዝቡ ገብቶ አንተ እንዳትወጣ ማለት ነው።

ቀ. ተጀምሮ እስኪጨረስ ዐይኖችህን አትጨፍን ወይም ደግሞ የግድ ሕዝቡን ዐይኑን አስጨፍነህ ፕሮግራሙን መጀመር እንዳለብህ አታስብ።

በ. ኢ-መደበኛ የሆነ አለባበስና የጸጉር እስታይል የሕዝቡን ትኩረት አሉታዊ በሆነ ሁኔታ ሊስብ ስለሚችል ተገቢ አለባበስ ይኑርህ።

## ማጠቃለያ

የጉባኤ አምልኮው ጊዜ በተለይም ሕዝቡ በኅብረ ዝማሬ እግዚአብሔርን የሚያወድስበ ትና ወደ ጥልቅ አምልኮ ገብቶ በመንፈስና በእውነት እግዚአብሔርን የሚያመልክበት ጊዜ እጅግ የከበረና ከሁሉም የላቀው ጊዜና አገልግሎት ነው። የጉባኤ አምልኮው ጊዜ ችግር ከገጠመው ሌሎቹ አገልግሎቶች ሁሉ ችግር ይገጥማቸዋል። ሰባኪው ተለቅቆ አይሰብክም፤ ሕዝቡም ተለቅቆ አያመልክም። ምክንያቱም የጉባኤ አምልኮው ዋና ዓላማ ጌታን በጋራ ማምለክ በመሆኑ ዋናው ዓላማ ከተሳተ ሌሎቹም ውጤታማ ሊሆኑ ስለማይችሉ ነው። ስለዚህ የጉባኤ አምልኮ አገልግሎትና የጉባኤ አምልኮ ጊዜ ትልቅ ዋጋ ያላቸው ስለሆኑ አክብረን ልንይዛቸውና በመረዳትና በእውቀት ልናስኬዳ ቸው ይገባል።

‹‹እግዚአብሔር አምላካችሁን ታመልኩታላችሁ፤ እርሱም እህልህንና ውሃህን ይባርካል፤ በሽታንም ከመካከልህ አርቃለሁ፣ ምድርህ የምትጨነግፍ አትሆንም፣ የዘመንህን ቁጥር እሞላለሁ፤ የጠላቶችህን ጀርባ ታያለህ›› (ዘፀአት 23፡ 25)።